

# ምዕራፍ አራት

# ካሪዝማዊ ቀውሶች

> ልክ እንደ ሌሎች በቤተ ክርስቲያን የነበሩ ኃይለኛ ንቅናቄዎች ካሪዝማዊ ተሃድሶም የራሱ ልዩ አደጋዎች አሉት። ደራሽ ወንዝ አገር ማጥለቅለቅ ብቻ ሳይሆን በየዳርቻው የሚጥላቸው ቆሻሻዎችም ይኖራሉ። ኤድዋርድ ኦኮነር እንዳመለከተው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ምንም እንኳ ከስሩና ከመጀመሪያ ግፊቱ የመንፈስ ቅዱስ ስራ ቢመስልም በከፊል ከመንፈስ ዕቅድ ጋር የሚሄድ የሚመስል ውስብስብ የሰው ጉልበት፣ በከፊል ደግሞ ከዚህ መስመር የሚወጣ የሚጋጭና የሚቃረንም ነው። ማንኛውም የእግዚአብሔር መልካም ስጦታ ለመጥፎ ግፊትም ሆነ በተሳሳተ መንገድ ተግባር ላይ ሊውል ይችላል። ...በሰዎች ባህርይና በቤተ ክርስቲያን ድርጅት ላይ የበላይ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ብዙ ጊዜ በኛ ዕቅድና መርሐ ግብርም ሆነ ከዚያም ባለፈ መንገድ ይሰራል። ይሁን እንጂ ያልተጠበቀ እሳታዊ ስራውን መጠበቅ ያለብን በምድጃው ውስጥ መሆን አለበት። የጸጋ ስጦታዎች እንደሌሉ መቁጠር ወይም ማስወገድ አግባብ አይደለም። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ያዘዘላቸው መድኃኒት የጸጋ ስጦታዎችን ባህርይና ዓላማ መረዳትን ነበር። ቀዶ ጥገናና የተበላሸውን ብልት መቁረጥን አልደገፈም ነገር ግን (የሰጣቸው) በስርዓት የሆነ አጠቃቀምን ልምምድ ሕክምና ነበር።[1]

ኢሬኔዎስ የተባለው ከ130-200 ዓ.ም. የኖረው ሃሳዊ ትምህርቶችን አጥብቆ ይቃወምና ይጽፍ የነበረው ሰው ስለ ስህተት ትምህርት መልክ ሲያስረዳ፤ "በእውነቱ ስህተት ወዲያው ታይቶና ታውቆ እንዳይጋለጥ ዕርቃኑን ከቶ አይገለጥም። ነገር ግን መስህብነት ያለውን ልብስ በብልሃት ለብሶ ከውጪ አምሮ የሚሞኝ ሰው ካገኘ ለማታለል ከእውነትም የበለጠ እውነት መስሎ ነው የሚታየው።"[2] ብሎ ነበር። ስህተት መቼም ስህተት መስሎ ቀርቦ አያውቅም። ሰይጣን የሚያምኑትን እንኳ እስኪያስት የሚደፍረው ሰይጣንነቱን በመግለጥ ሳይሆን የብርሃን መልአክን በመምሰል ነው። ሃሳዊ ትምህርቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገቡት ወይም በጓሮ በር ነው ያለዚያም የቅዱስ ቃሉን ካባ ለብሰውና መንፈሳዊ ቋንቋን ጎርሰው ነው እያሳሳቁ የሚወስዱት።

የምዕመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ያቃወሱና ላልዳኑም ሰዎች የማሰናከያ ዕንቅፋት የሆኑ አንዳንድ አዋኪ ትምህርቶችና ልምምዶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መግባታቸው የዘመናችንም እውነት ነው። በተለይም በመንፈስ ቅዱስ ስም ሰዎች የመሰላቸውን ሲሉና ሲያደርጉ መመልከት የተለመደ ሆኗል። እውነተኛው በሃሰተኛው መንፈሳዊው በስሜታዊው እየተሸፈነ ሲመጣ ማየትም እየተለመደ መጥቷል። የእግዚአብሔር ቃል በምንም ነገር ከተለወጠና ቦታው ከቃሉ ላነሰ ለማናቸውም ነገር ከተለቀቀ ቤተ ክርስቲያን አደጋ ላይ መሆኗን ማወቅ ይገባታል። ቃሉ ሙሉ ነው፤ የሚጨመርበት ነገር ካለ ጎዶሎ ነው ማለት ነው። ቃሉ የማይደግፈውና በቃሉ የማይመረመር ማናቸውም ነገር የክርስቶስ አካል ወደሆነችው ወደ ቤተ ክርስቲያን ከገባ ነቀርሳ ሆኖ ችግር መፍጠሩ ይፈጥን ወይ ይዘገይ እንደሆነ እንጂ አይቀርም።

ኢሬኔዎስ እንዳስተዋለው የስህተቶችን አሳች መልክ ማወቅና መጠንቀቅ ይገባናል። በኢሬኔዎስና በኛ ዘመን መካከል ያለው ልዩነት ቢኖር የጊዜ ልዩነት ብቻ ነው። ሰይጣንም ሆነ አሰራሩ አልተለወጡም። እንደ ገላትያ ምዕመናን ወደ ሌላ ወንጌል ፈጥኖ ዘወር ማለት እንዳይኖር ጥንቃቄ ያሻል። በዚህ ክፍል የምንመለከተው እነዚህን ስህተቶችና አሰራራቸውን የአቅጣጫቸውንም አዝማሚያ ነው።

በዘመናት ሁሉ የክርስትናን ሕይወት ከአካላዊ ልምምድ ጋር ብቻ በማያያዝ መንፈሳዊ ጣዕሙን ያበላሹ ንቅናቄዎች አልጠፉም። በአንጻሩ ደግሞ ክርስትና በምንም ዓይነት አካላዊና የሚታይ መስክ መገለጥ እንደማይገባው በማሳየት የምነናና የብህትውና ኑሮን የሚደግፉ ንቅናቄዎችም ነበሩ። ሁለቱም አመለካከቶች ሚዛን ካልጠበቁ ስህተት መሆናቸው ይበልጥ ጉልህ መሆኑ አይቀርም። በዚህ ዘመን ከብህትውናዊው ልምምድ ይልቅ ስጋዊውና ስሜታዊው ወደ ቤተ ክርስቲያን በመግባት ሲያናጋት ይታያል። ከታመሙ በኋላ ለመዳንንና ለማገገም የሚወስደው ጊዜ፥ የሚወጣው የገንዘብ፥ የጊዜና የስሜት ኪሳራ ሁልጊዜም ትንሽ አይሆንም። ቀድሞ ከትባት መውሰድ ግን ከሚመጣ ወረርሽኝ ብቻ ሳይሆን በኋላ ከሚደርስ ከብዙ መዘዝም ሊያድን መቻሉ እውነት ነው።

ወደ ዝርዝር ሃሳቡ ከመሄዳችን በፊት በዚህ ክፍል የተጠቀሱ ቃላትን በተሳሳተ መንገድ ላለመመልከት ምንነታቸውን ማጤን የሚያሻ መሆኑን ለማስታወስ እወዳለሁ። የቃላቱ አጠቃቀም በዐውዱ ውስጥ ሆኖ ትክክለኛውን አሳብ ማስተላለፍ እንደሚችል ተስፋ አደርጋለሁ። እንዲሁም በእንግሊዝኛ 'ካሪዝማቲክ' እና 'ፔንቲኮስታል' የሚባሉት ቃላት የእንግሊዝኛ ቅጽል ይሁኑ እንጂ መሠረታቸው እንግሊዝኛ አይደለም። በአማርኛ እየተጠቀምን ያለነው ይህ ቃል ባዕድ ቢሆንም አሳቡ ግን ባዕድ አይደለምና ለመረዳት እንደማያዳግት

ግልጽ ነው።

ካሪዝማ ማለት በግሪክ ቋንቋ የጸጋ ስጦታ ማለት ሲሆን ካሪዝማዊ ንቅናቄ ማለት የጸጋ ስጦታዎችን መገለጥ የሚያጎላ ንቅናቄ ማለት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ የጸጋ ስጦታ የሌለው ማንም ክርስቲያን የለምና ክርስቲያን ሁሉ ካሪዝማዊ ነው። ነገር ግን እነዚህ እንቅስቃሴዎች ራሳቸውን እንዲያ በመጥራት ከሌሎች የተለዩ መሆናቸውን በማሳየታቸው በዚህ ስም ተጠርተዋል። ቃሉን በጤናማው አጠራርና በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳቡ ከተጠቀምንበት ትክክለኛ አባባልና ሁሉንም አማኝ የሚያቅፍ ሲሆን በጠባቡና ንቅናቄውን ብቻ በተመለከተ ከተጠቀምን ግን ራሳቸውን ከሌሎቹ የተለዩ የሚያደርጉትን ማኅበሮች እንቅስቃሴዎችና ሰዎቻቸውን የሚመለከት ይሆናል። በዚህ ክፍል የምንመለከተው ሁለተኛውን ነው።

ጴንጤቆስጣዊ የሚለው ቃል ደግሞ ይህን ይመስላል። ጴንጤቆስጤ ማለት በግሪክ ቋንቋ ኀምሳኛ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ከፋሲካ በኋላ አርባ ዘጠኝ ቀናት ተቆጥረው በኀምሳኛው የሚከበረው የሰባቱ ሱባዔ በዓል ነው። (ዘዳ.16:10) በአዲስ ኪዳን ከፋሲካ በኋላ በኀምሳኛው ቀን በዓል ወይም በበዓለ ኀምሳ ዕለት መንፈስ ቅዱስ ወረደ። በአብ የተሰጠው የተስፋው ቃል ፍጻሜም በመሆኑ በዕለቱ በቤተ ክርስቲያን ማለትም በአማኞች ውስጥ ማደርና ቤተ ክርስቲያንን ማነጽ፥ መምራት፥ ማስታጠቅ፥ ለክርስቶስም ምጽአት ማዘጋጀት ጀመረ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ ስለሚኖር መንፈስ ቅዱስ ያለውና የሌለው ክርስቲያን የሚባል ነገር የለም።

ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴዎች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ሁሌም የሚስተዋሉ ቢሆንም እንደ ንቅናቄ የምናገኛቸው ግን ከተሃድሶው ዘመን በኋላ ነው። ጴንጤቆስጣዊ ንቅናቄ ማለት የጴንጤቆስጤው ዕለት ክስተት ዛሬም ይደገማል በማለት ይህን የማስተማር፥ የመለማመድና የማለማመድ ትምህርት ነው። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንደተዘገበው ጴንጤቆስጣዊ ንቅናቄዎች እሁለት ቦታ ይመደባሉ፤ እኒህም የቀድሞው ሁነኛ ወይም ዓይነተኛ ጴንጤቆስጣዊ ንቅናቄ (classical pentecostalism) እና ዘመናዊው ጴንጤቆስጣዊ ንቅናቄ (neo-pentecostalism) ናቸው። ይህ ሁለተኛው ዓይነቱ ነው ካሪዝማዊ ንቅናቄ ተብሎ የሚታወቀው። ይህ ንቅናቄ ቀደም ሲልም ከፕሮቴስታንት ተሃድሶና ከማግስቱም ጀምሮ ቢታይም በዚህ ክፍለ-ዘመን መግቢያ የተከሰተው የአዲሱ ጴንጤቆስጣዊ (neo-pentecostal) አዲስ እንቅስቃሴና ከክፍለ-ዘመኑ አጋማሽ ጀምሮ በጣም የተጋነነው ካሪዝማዊ ተሃድሶ (charismatic renewal) ከስጦታዎቹ በጥቂቶቹ ላይ በመመርኮዝና ሌሎችም አዳዲስ ትምህርቶችን በማዘል ላይ ያተኮረ ነው። የመጀመሪያው ዓይነቱ ንቅናቄ

ጤናማውና ቤተ ክርስቲያን ለመንፈስ ቅዱስ አሰራር በሯ ዝግ መሆን እንደሌለበትና እንዲያውም ንቁ መሆን እንዳለባት የጸጋ ስጦታዎችም ዛሬም ህያው እንደሆኑና ሊታዩም እንደሚገባ ያስተማረ ከተሃድሶው ዘመን ጀምሮ የታየ ትምህርት ነው። መንፈሳዊ በሚመስል ስሜት መክንፍና የተለያዩ የስህተት አሰራሮች ጎልተው መታየት የጀመሩት ግን በዘመናዊው ማለትም በተሃድሶው ዘመንም ሆነ በዚህ በ20ኛው ምዕተ-ዓመት መጀመሪያ እና ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በተለያዩ ቦታዎች ከተቀጣጠሉት የካሪዝማዊ ንቅናቄ ትምህርቶች ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ከመስመር የወጡ ቡድኖች ምን ይህል ከእውነቱ በመራቅ ፖለቲካዊና ኢ-መንፈሳዊ ቅርጽ እንደያዙ በትንሹም ቢሆን ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖሩን ስናይ ተመልክተናል።

አንዳንዶች ካሪዝማውያን ከጸጋ ስጦታ ወይም ከአንድ ልምምድ ጋር እንዳይሆን ሆነው ተጣብቀው ይቀራሉ። ይህን ነገር ካቶሊካዊው ጴንጤቆስጣዊ ምሁር ኤድዋርድ ዲ. ኦ'ኮነር 'በሽታ መሳይ ነገር' ብሎታል ስሙንም 'ካሪዝሜኒያ' ብሎታል።[3] ዘመናዊው ካሪዝማዊ ንቅናቄ የመጀመሪያው የክላሲካዊው ፔንቲኮስታሊዝም ቅጥያ ይምሰል እንጂ በብዙ ረገድ ከቅይዱ የወጣ ነው። ይህ ንቅናቄ የተጸነሰው፥ የተወለደውም ሆነ ያደገውም በምዕራቡ ዓለም ነው። ለማናቸውም ንቅናቄ ቅርጽ የሚሰጠው ከባቢ ከተቆረቆረበት ጊዜና ቦታ የሚወረስ በመሆኑ ለዚህም ንቅናቄ ይህ እውነት የማይቀር ነው። ይህ ንቅናቄ እራሱን የቻለ አንድ ቤተ ክርስቲያን ወይም ማኅበር ሳይሆን በአግድሞሽ ብዙዎችን የአብያተ ክርስቲያናት ማኅበሮች ወይም ዲኖሚኔሽን ያቋረጠ ንቅናቄ ነው። ሁነኛው ወይም ክላሲካዊው ፔንቲኮስታሊዝም ለእግዚአብሔር መንፈሳዊ አሰራር ደንዝዘው የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ይነቁ ዘንድ እንደቀሰቀሰውና እንዳነቃቃው ሳይሆን ይህኛው በብዙ ቦታዎች በነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ መከፋፈልንና መለያየትን የፈጠረ ንቅናቄ ነው። በውጤቱ አዲስ ማኅበር ይፈጠራል ወይም የተወሰኑት ተለይተው ወደ ሌላው ይሄዳሉ። የሌሎች ነባር አብያተ ክርስቲያናትም ምዕመናንን ጎዶሎ እንደሆኑና ሙሉ መሆን እንደሚያስፈልጋቸው በመንገር መውሰድ የንቅናቄው አንድ አንክን ነው። እንዲህ ሲሆን ፍቅር ይቀዘቅዛል አካልም ይፈረካከሳል።

አንዳንዶች ክርስቲያኖች ወደነዚህ የተሳሳቱ ልምምዶች ውስጥ የሚወሰዱት በየዋህነት ነው። ከተገባ በኋላ ደግሞ ስህተት ነው ብሎ መቀበል ከይሉኝታም ከኩራትም የተነሳ ይከብዳል። ከነዚህም ይልቅ በስህተት ውስጥ መኖርን ማመንና መቀበል ለልብ እሺ አይልም። አንዳንዶቹ ትምህርቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካባ ስለሚደርቡ ውስጣቸው አይታይም። ውስጥ ካልተገባ ደግሞ ማንነታቸው አይለይም። ስህተትነታቸውም በጭራሽ ሳይታይ ይቆያል ወይም ይኖራል። ያለንበት ጊዜ የመጨረሻው በመሆኑ የተገኘውን ሁሉ

ከመቀበል ይልቅ እንደ ቤሪያ ሰዎች ቆፍጣና የቃሉን ምንነት የምንመረምር ሰው መሆን ይገባናል። ካሪዝማዊ ንቅናቄዎች መጽሐፍ ቅዱስን ሲመረምሩ እጅግ መራጭ ናቸው። ብዙዎቹ እንደሚሉት ወደ አንድ የማያዳግም ልምምድ ስለደረሱ ቃሉን ሲተረጉሙ ከዚህ ልምምድ በመነሳት ነው። መሆን የነበረበት ግን ያ የነርሱ ልምምድ ራሱ በቃሉ ተፈትኖ ማለፍ ነበረበት። ስለዚህ ነው ከሐዋርያው ጳውሎስ አጠቃላይ ትምህርቶች ይልቅ በሐዋርያት ሥራ ላይ ትኩረት የሚደረገው ወይም ከክፍለ ምንባቡ ተነቅለው በወጡ ጥቅሶች ላይ ትምህርቶቹ የሚመሠረቱት። ሙሉው የእግዚአብሔር ምክር በከፊሉ ከተለወጠ ለማንም ቢሆን ችግር መፈጠሩ የማይቀር ነው። ጀምስ ሲ. ሉገን እንዳለው ከካሪዝማዊ ክርስቲያኖች ጋር ያለው ችግር እነዚህ ወገኖች ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆናቸው ሳይሆን በበቂ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያለመሆናቸው ነው።[4]

እነዚህ ስህተቶች ሁለት መልክ አላቸው፤ አንደኛው ልምምዳዊ ሲሆን ሁለተኛው ትምህርታዊ ነው። ከልምምዶቹ አንዳንዶቹ በድንገት ወይም ለዚያ ጊዜ ብቻ የተደረጉ እንኳ ቢሆን በኩረጃ ይባዛሉ። ከትምህርቶቹም አንዳንዶቹ በአንድ ወቅት በስህተት ቢነገሩም ሰሚ ጆሮ ውስጥ ይገቡና ተባዝተው ካልተጠበቀ ሁኔታ ላይ ይደርሳሉ። እነዚህን ስህተቶች በሙሉ በእያንዳንዳቸው መዘርዘርና መጨረስ ይከብዳል። ከልምምዶቹ መካከል ለምሳሌ 'በሰመመን ውስጥ መጥፋት' ወይም ሰዎች በመገንደስም ሆነ በሌላ ጊዜ ወደ ተመስጦ ውስጥ በመግባት የሚሰጥሙበት ልምምድ አለ። 'ቅዱስ ሳቅ' የሚባል ሌላ ደግሞ አለ። ይህ ሳያቋርጡ መሳቅ ነው። ልክ እንደተኮረኮሩ ማለት የማይታይ እጅ እንደኮረኮረው ሰው ሆኖ ባለማቋረጥ ከት ብሎ መሳቅ ነው። ከመሳቅ ጋር መንከባለል፥ መዝለል፥ መደነስና ሌሎችም መሰል ክስተቶች አብረው ይታያሉ። ይህ መጽሐፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ ይህ ቅዱስ ሳቅ የሚባለው ከሁሉም መንፈሳዊ ከሚመስሉት ልምምዶች በጣም አዲሱ ነው። ትኩስ ፋሽን እንደማለት። በነገራችን ላይ የቆዩት እየተሰለቹ አዳዲስ ልምምዶችን መፈለግ የዚህ ንቅናቄ አንድ ባህርይ ነው። ልምምድ መሠረት በሆነበት እምነት ይህ ደግሞ የማይቀር ነው፤ ምክንያቱም ልምምድ እንደ ጌታ ቃል ራሱን በራሱ የሚያቆምበት ጉልበት የለውም። ወደ ሳቁ ስንመለስ ጠጋ ወይም ገባ ብለው ሲመረምሩት ይህ 'ቅዱስ ሳቅ' ቅዱስም አይደለም ሳቅም አይደለም። በእርግጥ እግዚአብሔር አፍንም ልብንም ምክንያት ባለው ሳቅ ይሞላል ደግሞም ውስጥን በልዩ ደስታና ሐሴት ይሞላል። ይህ በቃሉም ውስጥ በሚገባ ተዘክሯል። ነገር ግን የሞላና የታመቀ ስሜት ለማጉደልና ለማፍሰስ ተብሎ የሚደረግ ዓይነት የሰው ብቻ ነገር ወይም የሰይጣን ስራ የሚመስል ነገር ሲደረግ በጌታ ቃል ውስጥ አልተጠቀሰም። ከዚህም በተጨማሪ ማጓራትና በተለወጠና በልዩ ዓይነት ድምጽ ለምሳሌ እንደ ጅብ መጮህ፥ እንደ አንበሳ ማግሳት፥ እንደ ሌሎችም አራዊትና እንስሳት ያለ ድምጽ ማውጣት አለ። ይህን ደግሞ 'ቅዱስ ጩኸት'

ብለው ሰይመውታል። ዱሮ የሚታወቀው እንዲህ ያለው ጩኸት ሰይጣን የያዛቸው ሰዎች ሲጸለይላቸው የሚጮኹት ነበር አሁን ግን 'ቅዱስ' የሚባል ካባ ደርቦ እንደገና ወደ ጌታ ቤትና ሕዝብ መጣ! ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው የሰይጣንን አሳብ ልንስት አይገባንም። የእርሱ ስራ የሚካሄድበት ዋና መንገድ ማስመሰልና ማታለል ነው። መውረግረግ፥ ሳያቋርጡ መንዘፍዘፍና መንቀጥቀጥ፥ ሌሎችም ተቀራራቢ ልምምዶች ለብቻና ከላይ ከተጠቀሱት ጋር አብረውም ይሄዳሉ። በየጊዜውም አዳዲስ ነገሮችና ልምምዶች ከስር ከስር መቀፍቀፋቸውም ከመቼውም ይልቅ ገሃድ እየሆነ መጥቷል።

ከትምህርቶቹና ከቡድኖቹ መካከል ደግሞ ለምሳሌ ክርስቲያን መሞት የለበትም የሚሉት 'የተገለጡት የእግዚአብሔር ልጆች' የሚባሉት እንዲሁም ከንቅናቄዎችም መሃል 'የኋለኛው ዝናብ ንቅናቄ' የሚባሉት ለአብነት ሊወሰዱ ይችላሉ። ሁሉንም የስህተት ትምህርቶችና ልምምዶች፥ ንቅናቄዎችና ቡድኖች አንድ በአንድ መጥቀስና መጨረስ ባይቻልም ጥቂቶቹንና ጎላ ጎላ ብለው የሚታዩትን ግን መመልከቱ አስፈላጊ ነው። አንዳንዶቹ በጣም ያልተለመዱ ቢመስሉም መጠንቀቂያ ይሆናሉ። በዚህ ክፍል የምንመለከታቸው ቀውሶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው፤

- በመንፈስ መገንደስ

-"የቀባኋቸውን አትዳስሱ"

- ፊደልና መንፈስ ቃልና ኃይል

- የመገለጥና የጭንቅላት ዕውቀት

- እባብ ያዦቹና መርዝ ጠጪዎቹ

- ቃል-እምነት

- የአምልኮ ቀውስ

- የእምነት ቀውስ

-የልሳኖች ቀውስ

- የፈውስ ቀውስ

- የተዓምራት ቀውስ ("ሦስተኛው ሞገድ")

- የሐብት ቀውስ

- አዲሱ ቀውስ ("ቅዱስ ሳቅ")

## በመንፈስ መገንደስ

በካሪዝማዊ ንቅናቄዎች በተለይም በዘመናዊዎቹ መካከል ከሚታዩት ክስተቶች አንዱ በመንፈስ መገንደስ እየተባለ የሚታወቀው ነው። ይህ ክስተት ሰዎች ኀሊናቸውን ስተው እመሬት ላይ የሚዘረሩበትና ሲነቁ እራሳቸውን እወለሉ ላይ (ሌላም ማናቸውም ቦታም ሊሆን ይችላል) የሚያገኙበት ልምምድ ነው። በዚህ ልምምድ የተገነደሱት ሰዎች እንደሚሉት በማያስተውሉት መንገድና በማያስታውሱት ጊዜ አዕምሮአቸው ባዶ እንደሚሆንና ጉልበታቸውም እንደሚከዳቸው ከዚያም ሳያውቁ እንደሚወድቁና ራሳቸውን እመሬት ላይ እንደሚያገኙት ይናገራሉ። አንዳንዶች ደግሞ ኃይለኛ የሆነ የማያውቁት ነገር እንደገፋቸውና ሊቋቋሙት ስላልቻሉ ብቻ እንደወደቁ ይናገራሉ። አንዳንዶች እርግጠኛ በመሆን የጣላቸው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ይናገራሉ። አወዳደቃቸው አንዳንድ ጊዜ በግል ሌላ ጊዜ በቡድንና በበርካታ ቁጥር ነው። የሚወድቁት ሰዎች አወዳደቅ በራሳቸው፥ በሌሎች ወይም በዕቃዎች ላይ ጉዳት የማያመጣ እንዲሆን ተብሎ ደግሞ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአንዳንድ እንዲህ ያለ የመገንደስ ክፍለ ጊዜ በሚኖርባቸው ጉባኤዎች የሚወድቁትን የሚደግፉና የሚያጋድሙ፥ ቀሚሳቸው የሚገለብባቸውን ሴቶችን ደግሞ ጨርቅ ነገር በላያቸው የሚያነጥፉ አጋፋሪዎችም አብረው እንዲያገለግሉ ማድረግ ተጀምሯል።

ይህ በጥቅሉ አዲስ የሆነ ክስተት በዘመናዊው ካሪዝማዊ ወይም ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ውስጥ በተለያዩ ስሞች በመጠራት የሚታወቅ ክስተት ነው። ከስሞቹም 'በመንፈስ ኃይል ተመትቶ መውደቅ'፥ 'በኃይል ስር

መውደቅ'፥ 'በመንፈስ መሸነፍ' የሚሉ ይገኙባቸዋል። የዚህ ዓይነቱ ልምምድ በጥቂት ካቶሊካውያን መነኩሳት ታሪክና በአንዳንድ የፕሮቴስታንት የተሃድሶ ጉባዔዎች የታየበት ጊዜ ነበር። ለምሳሌ በጆን ዌስሊ አገልግሎት ታሪክ ውስጥ ይህን የመሰለ ክስተት ይገኛል። በ19ኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ በአሜሪካ በነበሩት የሚዳና የድንኳን ስብሰባዎች ታዋቂ አገልጋይ በነበረችው በማርያ ውድወርዝ-ኤተር ይህ ልምምድ ይጠበቅም ይደረግም ነበር። በነዚህ ጊዜያት ይወድቁ የነበሩት አማኞች ብቻ ሳይሆኑ ወደ ጉባዔው መጥተው የነበሩ አሿፊዎችም ጭምር እንደነበሩ አንዳንድ የጽሑፍ ምንጮች ያወሳሉ። በጊዜው የነበሩ ጋዜጦች ሳይቀሩ ሰዎች እንደሞተ በድን ሆነው እመሬት ላይ ይወድቁ እንደነበር እስኪጽፉ ድረስ ይታወቅ ነበር። በ20ኛው ክፍለ ዘመንም ይኸው ልምምድ በተለያዩ ጴንጤቆስጣዊ አገልጋዮች ዘንድ እንደነበረ ተመዝግቧል።

በዚህኛው ምዕት ዓመት ይህ ልምምድ እየፈለጉና እያሳደዱ የሚያገኙትም ነው የሆነው። ጥልቅና አስፈላጊም ልምምድ ተደርጎ ይወሰድ ጀመር። ብዙዎች የሚወድቁ ሰዎችም ሲወድቁ ከምንም ነገር ጋር ቢጋጩ ሕመሙ እንደማይሰማቸውም ይናገራሉ። ከዚህም ባሻገር ደስ የሚል ስሜት እንደሚሰማቸው ያወሳሉ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ወድቀው የሚቆዩት ሰዎች የሚቆዩበት የጊዜ ርዝመት ከጥቂት ሴኮንዶች እስከ ብዙ ደቂቃዎች ይለያያል። ጥቂት በሰዓት የተቆጠሩ ክስተቶችም ተነግረዋል። ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ይሁን እንጂ ኬኔት ሄግን የተባለው ሰው ስለ ማርያ ውድወርዝ ሲመሰክር ይህች ሴት እንደ ሐውልት ለሦስት ቀንና ሌሊት ደርቃ እንደቆየች ተናግሮ ነበር።

አንዳንድ አገልጋዮች ይህን እንደ መደነቂያ ሲጠቀሙበት ሌሎችን ራሳቸውን የበረከት መተላለፊያ ወፍራም አሸንዳ እንደሆኑ ያስቆጥራቸዋል። ሌሎች ደግሞ ወደነርሱ የሚመጣን 'መጥፎ መንፈስ' እንደሚጥል ዘበኛ አድርገው ትክክለኛ ባልሆነ አመለካከት ያዩት ነበሩ። ይህን ነገር እንደመቅጫ አድርገው ከተጠቀሙበት መካከል አንዱ ኬኔት ሄግን የተባለው ሰው ነው። አንድ ጊዜ የራሱ ባልሆነ አንድ ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግል 'ሌቪቴሽን' የሚሉት ከመሬት ከፍ የመደረግ ነገር ተፈጸመ። የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢና ሚስቱ እንዲሁም የሄግን የራሱ ሚስት ይህ ነገር ከእግዚአብሔር መሆን ያለመሆኑ ጥርጥር ውስጥ ገቡና ደፍረው ቀርበው ጠየቁት። በማግስቱ እየጸለየ ሳለም የእግዚአብሔር ቃል መጣለትና እነዚያን የተጠራጠሩ ሰዎች በትንፏ ጣቱ ብቻ እንዲነካቸው ተነገረው። ሄዶ እንደተባለው ሲያደርግም ሦስቱም ተገንድሰው ከመሬቱ ጋር ተጣበቁ። ሄግን ሚስቱን ለማንሳት ቢሞክር እንኳን ሰውነቷን እጇንም ማንሳት አቃተው። ቀጥሎም ሌላ ቃል መጣለት እንዲህ የሚል፥ 'ሄደህ በእያንዳንዳቸው ጎን ተንበርከክና እንዲነሱ ንገራቸው ከዚያም ይህ ነገር በእግዚአብሔር ኃይል መደረጉን አምነው መቀበልና ያለመቀበላቸውን

ጠይቃቸው' ተባለ። ከዚያም ካሙኑ በኋላ መጀመሪያ እንዳደረገው በትንሿ ጣቱ ነክቶ እንዲፈታቸው ተነገረውና ፈታቸው።[5] ይህ እንደዘመናችን ታላቅ ነቢይ እራሱን የሚቆጥር ሰው የእርሱን ቃል የተቃወሙ ወይም አልቀበልም ያሉ እንደሚቀጡና ቅጣቱም እንደነ ሃናንያና ሰጲራ ፍንግል ብሎ በመሞት እንደሆነም ተናግሮአል። እንዲያውም አንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ እዚያው እመድረኩ ላይ ወድቆ መሞቱንም ለእንቢተኞች ምሳሌ እንዲሆን ብሎ ተናግሮአል።[6]

ብዙ ጊዜ እንዲህ ያለው ነገር የሚደረገው ከፈውስ አገልግሎት ጋር አብሮ ነው። ለጥቂቶች እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ ማደንዘዣ ወግቶ በሽታውን ከውስጣቸው እያወጣ ያለ ነው የሚመስላቸው። የአዲስ ኪዳንን የድውያን መፈወስ ስንመረምር የዚህ ተቃራኒ ሆኖ እንደምናገኘው ግልጽ ነው። ሲጸኑና ሲንለብቱ፥ ሲቆሙና ቀና ብለው ሲያመስግኑ፥ ቃሬዛቸውን ለመሸከም ከተኙበት ሲነሱና የታወሩት ሲያዩ፥ ደንቆሮዎች ወዲያው ሲሰሙና ዲዳዎች ወዲያው ሲናገሩ እንጂ ከዚያ በፊት ወይም በፈውሳቸው ጊዜ ወይም ከዚያ በኋላም ቢሆን አዕምሮአቸውን ሲስቱ ወይም እመሬት ላይ ሲወድቁ ወይም ጉልበታቸው ሲከዳቸው ከቶ አናነብም።

ይህን ነገር የሚያካሂድ አንድ አገልጋይ አንድ ጊዜ ተጠይቆ ሲመልስ "አንዳንድ ጊዜ ጥሩ ትዕይንት እንዲሆን እኛው እንገፋቸዋለን አንዳንዱ ከእግዚአብሔር ጋር ጥሩ ግንኙነት ሳይኖራቸው ቀርቶ ያልወደቁ መሆናቸውን ሌሎች እንዳያዩባቸው ሲሉ እራሳቸው ይወድቃሉ፥ አንዳንድ ጊዜ ግን ከእግዚአብሔር የተነሳ ሰዎች ይወድቃሉ" ብሎ ነበር።[7] አንዳንድ ሰዎች ተጸልዮላቸው ያልወደቁ እንደሆነ እነዚህ መንፈሰ ጠንካሮችና አንገተ ደንዳኖች ለመንፈስ ቅዱስም የማይታዘዙና የማይሸነፉ ተደርገው ተወግዘው ይመለሳሉ። እዚህ ላይ ቆም ማለትና ሁለት የማያዳግሙ ጥያቄዎችን መጠየቅ አስፈላጊ ነው።

የመጀመሪያው ጥያቄ ይህ የመገንደስ ልምምድ በሰዎቹ ማለትም በሚወድቁት ሕይወት ውስጥ የሚፈጥረው ምን ገንቢና ዘላቂ የሆነ ነገር አለ? የሚል ነው። አንዳንድ ይህን የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ዋናው ቁም ነገር መውደቃቸው ሳይሆን ነገር ግን ከወደቁ በኋላ ወይም ወድቀው እያለ የሚሆነው ነገር እንደሆነ ይናገራሉ። ሰዎች ወድቀው እያለ ወይም ከወደቁ በኋላ ስለሆኑት ነገር ደግሞ የሚቀርቡት የልምምዱ መደገፊያዎች የሰዎች ምስክርነቶችና ልምምዶች እንጂ የቃሉ ማስረጃዎች አይደሉም። የሰዎች ልምምዶች ደግሞ ከሰው ወደ ሰው የሚለያዩና እምነታችንን መደገፍ የማይችሉ እግዚአብሔርንም ይህን ተናግረሃል ብለን እንደ ተስፋ ሰጪ ልንይዘው የማንችልባቸው ነገሮች ናቸው።

በ1ነገ.8:11 እና 2ዜና.5:14 የምናገኛቸው ሰለሞን ያሰራው ቤተ መቅደስ በተመረቀ ዕለት ያገለግሉ የነበሩት ካህናት ከእግዚአብሔር ክብርና ከደመናው የተነሳ ቆመው ማገልገል እንዳልተቻላቸው ተጽፏል። ስለመውደቅ የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ይህንን "መቆምና ማገልገል አልተቻላቸውም" የሚለውን ሐረግ ካህናቱ ወድቀው እንደነበር አድርገው ያስተምሩበታል። አንድ ሰባኪ አምልኮ መውደቅን እንደሚያመጣ ሲናገር ስለዚህ ቦታም ጠቅሶ እንዲህ አለ፤ ጥቅሱ ከስብከቱ በቀጥታ የተወሰደ ነው።

> ዎርሺፕ የእግዚአብሔርን ክብር አትራክት ያደርጋል። ሽማግሌዎቹ ቄሶች፥ ቀላውስቱ ተሰብስበው ሲጸልዩ ይላል የእግዚአብሔር ቃል ሲዘምሩ ሶሪ ሙዚቃ ሲ በሙዚቃ መሣሪያ ሲጫወቱ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ምህረቱ ለዘላለም ነውና እያሉ ሲዘምሩ ይላል የእግዚአብሔርም ክብር ደመና መጣ እነርሱም መቆም እስከማይችሉበት ድረስ ተንገዳገዱ ወደቁ። መቆም እስከማይችሉ ማለት እንግዲህ ካልቆሙ ተቀምጠዋል ወይም ወድቀዋል ማለት ነው ሌላ ነገር የለውም። መቆም እስከማይችሉ ድረስ የእግዚአብሔር ክብር በሕይወታቸው እንደመጣ ይነገራል። አንዳንድ ጥያቄ የሚፈጥሩብን ነገሮች አሉ ለምንድነው አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በሰዎች ላይ ሲመጣ ሰዎች የሚወድቁት?...አንድ ነገር እምነግራችሁ ነገር ምንድነው መውደቁ ምን ጥቅም አለው? ትላላችሁ፤ አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ይህንንም ዲስፓይዝ እያደረጉ ይናገራሉ አንድ ነገር ግን ልንገራችሁ ኢንተርቴይን ለማድረግ አይደለም ሚጥላችሁ ነገር ግን በሕይወታችሁ የሆነ ነገርን አኮምፕሊሽ ለማድረግ ነው እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን። ...የሰዎች መውደቅ ሳይሆን ትልቁ ነገር ወድቀው ከተነሱ በኋላ በሕይወታቸው የሚሆነው ነገር ነው።[8]

ብሎ ሰብኳል። መቆም አለመቻል ማለት የግድ መውደቅ ማለት ነው ካልን ይመስል ይሆናል። ነገር ግን የራሳችንን አሳብ በቃሉ ውስጥ መሳግና የፈለግነውን እንዲልልን ማድረግ ከቃሉ አስተማሪዎችና ሰባኪዎች የሚጠበቅ አይደለም። ብዙዎች ለዚያች ጊዜ ከሚሆን ስሚታዊ ነውጥና ጊዜያዊ እርካታ በቀር ለዘመንና ለዘላለም የሚሆን ነገር ከወደቁበት ይዘው እንዳልተነሱ ይናገራሉ በግልጽ የሚታይ ነገርም ነው። የሚፈጥረው ሌላ ነገር ካልኖረ ወድቆ መነሳት እስፖርታዊ ጅምናስቲክ ብቻ ሊሆን ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ መሆን የሌለበት ነገር ነው። ፈውስ ከኖረ ፈውስ ነው። መውደቅም፥ መንከባለልም፥ መጋጨትም፥ መገለብም ሳይኖር እግዚአብሔር ሊያደርገው ከወደደ የሚያደርገው ነገር ነው። መገንደስ ከፈውስ ጋር ከተያያዘ መገንደስ

ሳይኖር የተደረገው ፈውስ ጎዶሎ አይደለም። የተደረገው ነገር ሌላ በረከትም ቢሆን መውደቅ ያንን በረከት ሙሉ የሚያደርግበት የራሱ የሆነ አንዳች ነገር የለውም።

ሁለተኛው ጥያቄ ከመጀመሪያው ጥያቄ ይልቅ የበለጠና ትልቅ ግምት ሊሰጠው የሚገባው ነው ያም በእውነት ስለዚህ ነገር መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው ትምህርት አለ ወይ? የሚል ነው። አጭርና ግልጽ የሆነው መልስ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ዘመናዊውን በእጅ በመንካትና በመግፋት በትንፋሽ እፍ በማለትና ልብስን አውልቆ በመወርወር በመሳሰሉትም መንገዶች የሚደረገውን መገንደስ በመደገፍ የሚናገርበት አንድም ክፍል የለም! ይሁን እንጂ ይህንን መገንደስ የሚባለውን ነገር በሚያስተምሩ ሰዎች የሚጠቀሱ አንዳንድ ጥቅሶች አሉ። በጠቅላላው አዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ ነገር የታየባትም ሆነ ትምህርቱ የተሰጠባት ቤተ ክርስቲያን የለችም። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ልምምድ እንደጤናማ የክርስትና ሕይወት ክፍል አድርጎ ከቶ አያስተምርም። ይህን የመውደቅ ትምህርት የሚያራምዱ አስተማሪዎች የሚጠቅሷቸው ጥቅሶች ከዚህ ዘመናዊ ልምምድ ጋር የሚዋደዱ አይደሉም። በተደጋጋሚ የሚጠቀሱትን ጥቅሶች መመልከቱ አስፈላጊ ስለሚሆን እንያቸው።

በዘፍ.15:12-21 አብራም ከባድ እንቅልፍ እንደመጣበትና እዚያ ውስጥ ሳለ እግዚአብሔር ስለወደፊቱና ስለሚቀጥለው ትውልድ እንደተናገረው ተጽፏል። የእግዚአብሔርና የአብራም ግንኙነት የተለየ ግንኙነት ነበር። በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ እግዚአብሔር ለአብራም በራዕይ ተገልጦለት ነበር። እዚህ ቦታ ግን እግዚአብሔር አምላክ የተገለጠው አካላዊነት ባለውና በሚያስደነግጥ ሁኔታ ነበር። ያ ስፍራ የሁለቱ የቀጠሮ ቦታ ነው። አብራም አድርግ የተባለውን አድርጎ እየጠበቀ ነው። እግዚአብሔር የሚያስፈራ ግርማ ያለው አምላክ በመሆኑና እርሱንም አይቶ በሕይወት የሚኖር ባለመኖሩ ጌታ ራሱ ነው በመለኮታዊ ጥበቡ ለዚህ ልዩ ቀጠሮ ያዘጋጀው። ስለዚህ ይህ የአብራም እንቅልፍ መገንደስን አይመስልም። መገንደሳቸው የአብራምን መሳይ ነው የሚሉት በቀጠሯቸው ቦታና ጊዜ እንጂ በመድረክና በሰው እጅ አማካይነት መውደቅ የለባቸውም።

በዘኁ.24:4 የቢዖር ልጅ በላቅ የገዛው በለዓም የተባለው ቃልቻ ሲናገር "የወደቀው ዐይኖቹም የተከፈቱለት..." ብሎ ነበር። ይህን ሲል መልአኩ እንደተጋፈጠውና ጌታም የራሱን ታላቅነትና የእስራኤልን ውበት እንዳሳየው መናገሩ ነው። በለዓም ከመልአኩ ጋር ከመጋፈጡ በፊት የእግዚአብሔርን ክብርም ሆነ የሕዝቡን ክቡርነት አላየም። እንዲያውም መተቱን ሊደግምባቸውና ሊረግማቸው ነበር ተጠርቶ የሄደው። በዘኁ.22:31 መልአኩን

እንዳየ በግንባሩም እንደወደቀና እንደሰገደ ተጽፏል። የዓላማው አቅጣጫ የተለወጠው ከዚያ በኋላ ነበር። ሊረግም የተጠራው የባረከውና አህያዋ ያላየችውን ያላየው 'ዕውር' የልዑልን ራዕይ ያየው ከወደቀና ዓይኖቹም ከተከፈቱለት በኋላ ነበር። ይህ መውደቅ መልአኩን ከማየት ጋር የተያያዘ ከመሆኑ ሌላ በሚወድቅበት ጊዜ በለዓም 'አንድ ቃልቻ' ብቻ እንጂ የእግዚአብሔር ሰው አልነበረም። ስለዚህ ይህ የቃልቻው መውደቅ ዘመናዊውን መገንደስ አይመስልም፤ አይደለምም።

በ1ሳሙ.19:20 ሳሙኤል በነቢያት ጉባኤ መካከል 'ቆሞ' የሚለውን አሳብ አንዳንድ የመገንደስ አስተማሪዎች ሌሎቹ የነቢያት ጉባዔ ወድቀው ወይም ተገንድሰው እንደነበር ያስተምራሉ። ይህ ቦታ የዚህ ዓይነቱን ትምህርት በግልጽ አያስተምርም። በግምት ደግሞ የወደድነውን አሳብ በቃሉ ውስጥ የማስገባትና የመጨመር መብት አልተሰጠንም። በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ሳኦል ትንቢት የተናገረበትንና ራቁቱን ወድቆ ቀንና ሌሊት የተጋደመበትን ታሪክ እናገኛለን። ሳኦል ትንቢት ሲናገር ይህ ሁለተኛ ጊዜው መሆኑ ነው። የመጀመሪያው ልክ ሊነግስ እንደተቀባ ነበር። በዚህኛው ጊዜ ግን የዳዊት ዝና እየገነነ በመምጣቱ በቅናት በግና ሊያስይዘው ወደ አርማቴም ወደ ሳሙኤል ዘንድ ሦስት የመልዕክተኞች ቡድን አከታትሎ ሦስት ጊዜ ሰደደ። የተላኩት አብረው ትንቢት ይናገሩ ጀመር። በመጨረሻ የሳኦል ቁጣ ነደደና እራሱ ተነስቶ ሳሙኤልንም ዳዊትንም ፍለጋ ገሰገሰ። ምንም እንኳ ሳኦል ራሱ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተቀባ ቢሆንም ሳሙኤልና ዳዊት የእግዚአብሔር ምርጦች ናቸውና ይህ ንጉስ እንደ አውሬ አዳኝ ሊያድናቸው አይገባውም ነበር። ግን ደፍሮ አደረገ። ዳዊትን ግን ሊያድነው ወዶ እግዚአብሔር ሳኦልን በወደደው 'ልጓም' ሲይዘው እናያለን። መንፈስ ወርዶበት የመጣበትን ዓላማ አስጥሎ የዚያን ተቃራኒ ሲያደርገው እናያለን። ራቁቱን ወድቆ ተጋድሞ ቀኑንም ሌሊቱንም ውሎ አደረ። ይሁን እንጂ የሳኦል የከፋ ልቡ በሆነው ነገር አልተበገረም። ቆይቶ ደግሞ እንደገና ማሳደዱ ሲያገረሽበት እናያለን። ሳኦል በእግዚአብሔር እንደተነበና ጥርጥር የለውም ግን የሆነ አይመስልም ነበር። ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተዳስሰው ግን ተመልሰው የበፊቶቹን እንርሱነታቸውን ሲሆኑ ያሳዝናል። ሳኦል እራቁቱን ውሎ ያደረበት ሁኔታ ከማሳደዱ እንዲያርፍ እግዚአብሔር የወሰደበት እርምጃ ነውና ዘመናዊውን መገንደስ የማይመስል ነው። በአዲስ ኪዳንም ጌታ ሳውልን ያገኘው ከዚህ ጋር ተቀራራቢ በሆነ ሁኔታ ነበር።

ሕዝ.1:28-2:1 እንደሚነግረን ሕዝቅኤል ራዕዮቹን በሚያይበት ጊዜ ከጌታ ክብር ታላቅነት የተነሳ ይወድቅና ጌታም 'ተነስ' ይለው እንደነበር እናያለን። ሕዝቅኤልን መንፈስ ቅዱስ አልጣለውም እንዲያውም ከወደቀበት

በእግሩ አቆመው እንጂ። እነዚህ የጌታ ነቢያት የሆኑትን ነገር ከመገንደስ ጋር ማመሳሰል የነዚህን ሰዎች የከበረ አገልግሎትና የከበረው ቃል የተጻፈበትን ሁኔታ በውሃ እንደማቅጠን የሚያስቆጥር ነው። የሕዝቅኤልን መውደቅ ቴያትር ከሚመስለው በሰዎች ትንፋሽ ወይም በእጅ ግፍተራ ወይም እርግብግቢታ ከመውደቅ ጋር ማመሳሰል በእውነት የድፍረት አባባል ነው።

በአዲስ ኪዳንም የወደቁ ሰዎችን ታሪክ እናገኛለን። በማቴ.17:6 ከብሩሁ ደመና የመጣውን የአብን ድምጽ ሰምተው ሦስቱ ሐዋርያት ፈርተው በፊታቸው እንደወደቁ ተጽፏል። ጌታ ራሱ ቀርቦ እስኪዳስሳቸው ድረስ አልተነሱም ነበር። ተመሳሳዩን ታሪክ በሉቃ.9:32 ስናነብ ከዚህ ከዩት ግርማ የተነሳ እንቅልፍ እንደከበደባቸውም ተጽፏል። እነዚህ ጥቅሶች ከሚያስጨብጡን እውነት በመነሳት በመገንደስ ልምምድ ውስጥ የሚወድቁት ሰዎች የሚወድቁት የኢየሱስን ክብር አይተው ወይም የአብን ድምጽ ሰምተው እንደሆን ቢጠየቁ ይህ ጥያቄ እንደ ድፍረት መቆጠር የለበትም።

በዮሐ.18:6 "እንግዲህ እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ ወደኋላቸው አፈግፍገው በምድር ወደቁ"የሚል ጥቅስ ይገኛል። እነዚህ እዚህ ስፍራ የመጡት ጭፍሮችና የካህናትና የፈሪሳውያን ሎሌዎች ናቸው። ይህን እንደ ድጋፍ ጥቅስ አድርገን ልንወስድ እንደማይገባ ግልጽ ነው። ምንም መመሳሰል የለውም። ደግሞም እነዚህ ሰዎች የማያምኑ ከመሆናቸውም ሌላ መውደቃቸው በሕይወታቸው የፈጠረው ቅንጣት ታህል ለውጥ አልነበረም። የመጡት ኢየሱስን ሊይዙት ነበር፤ ከመጡም በኋላ ይዘውት ሄዱ እንጂ ጌትነቱን አምነው አልተከተሉትም።

በማቴ.28:4 ላይ ሌሎች በፍርሃት የተናወጡና እንደሞቱ የሆኑ ሰዎች እናገኛለን። እኒህ የመቃብር ጠባቂዎች ለምን እንደወደቁ መገመት ከባድ አይደለም። እዚህም ላይ ሁለት ነጥቦችን መመልከት ጠቃሚ ነው። የመጀመሪያው ዘበኞቹ የማያምኑ መሆናቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ድንጋጤአቸውን የከበበው ትዕይንት ልዩ መሆኑ ነው። እንደ መብረቅ ያለ መልክና እንደበረዶ የነጣ ልብስ የለበሰ የጌታ መልአክ መውረዱ መሬት መናወጧና መልአኩም ድንጋዩን ማንከባለሉ አስደንጋጭ ነገር ነው። እነዚህ ሰዎች እንደሞተ የሆኑት ወይም የወደቁት ከው በሚያደርግ ድንጋጤ ደንግጠው እንጂ መንፈስ ቅዱስ ነክቷቸው አይደለም። አንዳንድ ድንጋጤ እንደሚጥል የማይካድ ነው።

አንዳንድ የመገንደስ አስተማሪዎች የሚጠቅሱት ሌላ ጥቅስ 2ቆሮ.12:2 ነው። ይህ ጥቅስ ጳውሎስ ወደ 3ኛ ሰማይ የተነጠቀበትን ታሪክ የተናገረበት ነው። መነጠቁ በስጋ ይሁን ያለስጋ ጳውሎስ እራሱም እንኳ አላወቀውም።

ስለዚህ መንገደስን ከጊዜያዊ የመነጠቅ ስመመን ጋር ማመሳሰል የጥቅሱን ዐውድ መሳትና ቃሉ የማይለውን ነገር እንዲል ማስገደድ ነው። ጳውሎስ የተነጠቀው በስጋ ከሆነና የዘመናችንም ተገንዳሾች ይህን እየተለማመዱ ከሆነ ስጋቸው ከሚወድቁበት መድረክ በተሰወረ ነበር። ጳውሎስ የተነጠቀው ያለስጋ ከሆነና እኒህም የእርሱን ፈለግ እየተከተሉ ከሆነም ሌላ ሰው ሊጸልይላቸውና ሊወድቁ ባላስፈለገም ነበር። በስጋም ይሁን ያለስጋ የጳውሎስ መነጠቅና ዘመናዊው 'የመውደቅ አገልግሎት' ሆድና ጀርባ ናቸው።

በሐዋ.9:4 ነገሩ ሲከሰትበትና በኋላ ደግሞ በሐዋ.22 እና 26 ስለራሱ ሲናገር የምናገኘው ጳውሎስ ወድቆ ነበር። አብረውት የነበሩትም ወድቀው ነበር። ይህንንም ከመንገደስ ልምምድ ጋር ልናገናኘው አንችልም በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ራሱ ክርስቲያን አልነበረም። ደግሞም የወደቀው እጅ ሲጫንበት ወይም ልብስ ሲጣልበት ወይም እፍ ሲባልበት ሳይሆን ከሞት የተነሳውና የከበረው ጌታ አስፈሪ ግርማ ተጋፍጦት ነው። በእንዲያ ያለው ግርማና ክብር ፊት ቆሞ የሚቆይ አሳዳጅ ሊኖር አይችልም።

ከላይኛው ጋር በሚቀራረብ ሁኔታ ሲወድቅ የምናገኘው ሌላው ሰው ሽማግሌው ሐዋርያው ዮሐንስ ነው። ዮሐንስ ስለ ጌታ ታስሮ ወደ ፍጥሞ ደሴት ተወስዶ በግዞት ይኖር በነበረ ጊዜ ታላቅ የመለከት የሚመስል ድምጽ ሰማ። አከታትሎም የሰው ድምጽ ሰማና የሚናገረውን ለማየት ዘወር አለ። ዘወር ሲል ያየው የማንነቱ ክብር በራዕ.1:13-16 የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ልጅ ክርስቶስን ነበር። በዚህ ክፍል የተዘረዘረው የሚያስደነግጥ ሞገስ ያለው የጌታ ማንነት ነው። 'ባየሁትም ጊዜ እንደሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ' ያለውን የዮሐንስን የዚያ ጊዜ ሁኔታ በመንፈስ ከመንገደስ ጋር ማመሳሰል በፍጹም አይገናኝም! አይሞከርምም። ሐዋርያው የወደቀው ተገንድሶ ጎሊናውን ስቶ ተመስጦ ውስጥ ገብቶ ራዕይ ሊያይ ሳይሆን ጌታን ክርስቶስን በአምላክነቱ ስለተመለከተው ብቻ ነበር። የሚያየውንማ ነገር ያየውና ራዕዩን የጻፈው የጌታ ቀኝ እጅ ከተጫነችበትና ከተነሳ በኋላ ነው።

በ1ቆሮ.14:25 በቤተ ክርስቲያን ልሳን ሳይሆን ትንቢት በሚነገርበት ጊዜ የማያምኑ ወይም ያልተማሩ ቢገቡ በልባቸው የነበረው ስለተገለጠ እግዚአብሔር በመካከላቸው መኖሩን ተናግረው ወድቀው እንደሚሰግዱ ተጽፎአል። ይህ መውደቅም ከዘመናዊው መንገደስ ጋር ዝምድና የለውም ምክንያቱም ይህ መውደቅ የአምልኮ ማለትም ክብርን ለእግዚአብሔር የመስጠት መውደቅ ነው። ምክንያቱም እነዚህ የሚያደርጉት መውደቅ የመስገድና ክብርን ለእግዚአብሔር የመስጠት እንዲሁም አውቆም የሚደረግ ነገር በመሆኑ ነው።

በመገንደስ ልምምድ የሚታየው ሁኔታ ክርስቶስን ከማየት የመነጨ አይደለም። ለነገሩ እርሱን ለማመንም ሆነ እምነታችንን ለማጎልበት እርሱን ማየት የለብንም እንጂ የሚታይ እንኳ ቢሆን በእንደዚያ ያለ የተወሰኑ እጅ ጫኝ አገልጋዮች ባሉበት መድረክ ብቻ መታየቱን ጌታችን እራሱም ሆነ ቅዱሳን ሐዋርያቱ አላስተማሩትም። እንዲያውም በተቃራኒው ሰዎችን ይዞ ሳያስቡና ሳይጠብቁ ሲያፈርጣቸው አንዴ ወደ ውሃ ሌላ ጊዜ ወደ እሳት ሲወረውራቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው ሰይጣንን ነው። (ማቴ.17:15፤ ማር.9:17-27) ይህ ልምምድ መጽሐፍ ቅዱስ የማይደግፈው ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ክርስቲያን ባልሆኑ ኃይማኖቶችና በሰይጣን አምላኪዎች ዘንድ የተለመደና የተወደደ የሚዘወተርም ነገር ነው።

አንድ ክርስቲያንና እግዚአብሔር የሚገናኙበት ሁኔታ እጅግ ውብ የሆነ ድንቅ ልምምድ ነው። ያም ሰው ያውቀዋል ነፍሱም ስጋውም ትለወጣለች። በእልፍኙ ውስጥ ይሁን በመስክ፣ በመንገድ ይሁን ወይም በወደደው ቦታ እግዚአብሔር ከልጆቹ ጋር ሊገናኝ ከወደደ ማንም አይከለክለውም። በአምልኮ መሃል ይሁን በስብከት ውስጥ፣ በመዝሙር ጊዜ ይሁን በጸሎት ሰዓት ብቻ ያቺ ጊዜ ዕፁብ ናት። እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያድስበት፣ የሚያንጽበት፣ እንባን የሚያብስበት ወይም በእንባ ውስጥ የሚባርክበት ለልብ የሚናገርበት ፍጹም የሆነን ነገር በልጆቹ ውስጥ የሚሰራበትን ጊዜና ቦታ ግን ሰዎች ተስማምተው አይወስኑለትም። ወይም መናፍስት ጠሪዎች እንደሚያደርጉት የሆነ ስርዓት ፈጽመው ምሱን አድርገውለት እንደሚጠሩት ተጠርቶ የሚመጣ አምላክ አይደለም። እርሱ የእውነት አምላክ የሚሰራውን የእውነት ስራ ከራሱና ከዚያ ሰው በቀር ማንም የሚያውቀው የለም። መንፈሳዊ ስራ ደግሞ የመንፈስ ስራ ማለትም የውስጥም ስራ ነው። ሌሎች የሚያውቁት ነገር ቢኖር ከዚያ በኋላ የሚኖረውን ታሪክ ነው።

እግዚአብሔር እርሱ የፈቀደውን ማድረግ የሚችል አምላክ ነውና ሰዎችን የፈለገውን ማድረግ አይሳነውም። ከፈለገ ጠቅልሎ ሊጥል፣ ከፈለገም ሊያሽከረክርና ሊያንከባልል ከፈለገም ያሻውን ሊያደርግ ይችላል። አይችልም የሚል አይኖርም። እግዚአብሔር ሰዎችን ሊጥል በሚችል እንዲህ ባለ መንገድ ፈጽሞ አይነካም አይገናኝም ማለት ሳይሆን ይህን ዘመናዊውን ግንደሳ የሚመስል ነገር በአዲስ ኪዳንዋ ቤት ክርስቲያን ውስጥ ስለማናይና ስነ-መለኮታዊም ሆነ ትምህርታዊ ወይም ልምምዳዊ መሠረትም ስለሌለው ለዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ይህን ትምህርት ማስተማር ለስህተት አሰራር ማጋለጥ ነው። ጌታ በጉባዔው ተገኝቶ የወደደውን ሊያደርግ ባለስልጣን ነው። ይሁን እንጂ ይህን ዘመናዊውን መሳይ መገንደስ በአዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት ባለመገኘቱ በጉባዔዎቻችን እንዲህ ያለው ለሰይጣናዊ አሰራር ያሚያጋልጥና በር የሚከፍት ልምምድ ሲኖር መጠርጠሩና መጠንቀቁ

አማኞችንም አሳልፎ ለመስጠት ያለመፍቀዱና እንዲህ ያሉትን አገልጋዮች ጀርባቸውን፥ ትምህርታቸውን ከዚህ በፊት የነበሩበትን አገልግሎትና ህይወታቸውን በተለይም ይህን ነገር መቼ፥ የትና እንዴት እንዳገኙት በግልጽ አውቆ ልምምዳቸው ለቃሉ እንዲገዛ እንጂ ልምምዳቸው ከቃሉ በላይ ስልጣን እንዳይኖረው ማድረጉ ለመሪዎች እጅግ ጥበብ ነው። በአገራችን ይህ መውደቅ በይበልጥ የተዛመተው በኛ አቆጣጠር በ1970ዎቹ አጋማሽና መጨረሻ ከገቡት ቪዲዮዎች በመቅዳት ይመስላል። አገልግሎትና ስጦታ እንደፋሽን የሚኮርጁት ከሆነ ስህተት ነውና በጣም ያሳዝናል! ስለዚህም መጠንቀቅም ይገባል። የጸጋ ስጦታ የሚታደሉት ስጦታ እንጂ የሚኮርጁት ነገር አይደለም።

በታወቁት የ18ኛው መቶ የመነቃቃት ሰባኪዎች በነ ጆናታን ኤድዋርድስ (1703 - 58) እና ጆርጅ ዋይትፊልድ (1714 - 70) አገልግሎቶች ወቅት ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ይወድቁ እንደነበር ከአገልግሎቶቻቸው የታሪክ ገጾች እናገኛለን። ይሁን እንጂ በነዚህ ሰባኪዎች አገልግሎት ዘመን ሰዎች ራሳቸውን ሰጥተው ሳይሆን የእግዚአብሔር ቅድስናና የነርሱ ኃጢአተኛነት በስብከቱ ጊዜ አስረግጦ ስለሚነገር ይህ እየታያቸው በኢሳ.6:5 ወይም በኢዮ.42:6 የሆነውን በሚመስል ሁኔታ ነበር እመሬት ላይ ይወድቁና ይዋረዱ የነበረው። የዚህንም ዓይነት የወቀሳና የንስሃ ስራ የሚሰራው ራሱ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን በቃሉ ውስጥ እናገኛለን። ይህ እጅግ ድንቅ የሆነ ስራ ነው። ቃሉ ሲሰበክ ሰዎች የጌታን ጌትነት አይተው የራሳቸውን በደለኝነት ተረድተው ሲወድቁ እንደማየት የመሰለ ግሩም ትዕይንት በአገልግሎት ውስጥ ያለ አይመስለኝም።

ዘመናዊው መገንደስ ግን ሰዎች አገልጋዩ ፊት ተኮልኩለው የሆነ ነገር ተብለውና ተደርገው የሚገነደሱት እንጂ የራሳቸውን ኃጢአተኝነት ተመልክተው ወይም የእግዚአብሔር ክብር ቅድስና አስበው የሚዋረዱበት አይደለም። እየሆኑ ያሉት ነገሮች እየሆኑ ያሉት እግዚአብሔር የጥቂቶችን ያለማስተዋል ለመርዳት ምናልባት አሰምረዋለሁ ምናልባት ከሚያደርገው በቀር ሰዎች አውቀው በስሜታዊ ግለት ወይም በይሉኝታ የሚያደርጉት ወይም የሚሆኑት ነው ወይም አንድ ያልሆነ ነገር የሆነ እየመሰላቸው በውሸታም ስሜት ተታልለው የሚሆኑት ነው፤ ካልሆነም ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሰዎች ከዋናው ነገር ወዳነሰውና ወዳልሆነው ነገር ዓይናቸው እንዲያተኩር የሚያደርግበት መሳሪያ ነው። ብዙዎች ወድቀው ኀሊናቸውን ስተው የቆዩ ሰዎች በሚነቁበት ጊዜ በመካከል የሆነውን አያውቁም ወይም አያስታውሱም። ብቻ በደፈናው እንደተባረኩ ይናገራሉ። በመካከል የሚሆኑበትና የሚቆዩበት ባዶ መሆን ወይም ባዶነት ደግሞ ከጥንታዊው የምስራቃውያን ኃይማኖትና ከዘመናዊው የዮጋ ትምህርት ብዙም የራቀ አይደለምና ጠበቅ ያለ ጥንቃቄ መውሰድ ያስፈልጋል። ሕይወትን ለዘለቄታ የማይለውጥ እንደፍም ውስጥ ብረት ግሎ ግለቱ ከዚያ

ጉባዔና ከዚያ ቀን የማያልፍ ልምምድ መንፈሳዊነቱና ሕይወትን የመገንባት አቅሙ የመነመነ ብቻ ሳይሆን የሌለም ነው ማለት ይቻላል።

ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያለውን ሰው-ሰራሽ ልምምድ ከቃሉና ካለፈው ታሪኳ ጋር እያስተያየች መቀበል የማይገባትን ለመጣል ሁሌም የተዘጋጀች ልትሆን ይገባታል። ጳውሎስ በ2ቆሮ.11:4 የቆሮንቶስን ምዕመናን ያስጠንቀቀውን ማስጠንቀቂያ ማስተዋል ተገቢ ነው። እነዚህ ሰዎች እየታገሱና እየተቀበሉ ያሉት ያልተሰበከላቸውን ሌላ ኢየሱስ ያላገኙትን ልዩ መንፈስ ያልተቀበሉትንም ልዩ ወንጌል ነው። አንዳንድ ምዕመናን የሚሳሳቱት ስህተት የየዋህነት ስህተት ነው፤ በጣም የሚያምኑት በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሚያስደስታቸው ሰው የተናገረውን ያደረገውንና የሆነውን በሙሉ ያለ አንዳች ጥያቄና ጥርጣሬ ይቀበሉታል። እንዲህ ያለውን ትምህርት የሚያስተምሩትም መጠራጠር ያለማመን መሆኑን ያለማመን ደግሞ ኃጢአት መሆኑን በመናገር በነዚህ ሰዎች ድካም ላይ ግፊት ይጨምሩበታል። እንደ እውነቱ ከሆነ ጤናማ የሆነ ጥርጣሬ አለ፤ አስፈላጊም ነው። ያለማመን የሚሆነው ጥርጣሬ ጌታን ራሱንና የተናገረውን ቃሉን የገባውንም ተስፋ ስንጠራጠር ነው እንጂ እንዲህ ያለው ጥርጣሬ እንዲያውም በተቃራኒው ትክክለኛ ጥርጣሬ ነው። ለማንም ክርስቲያን እግዚአብሔር ማስተዋልን የሰጠው የብርሃን መልአክ መስሎ የሚመጣውን ሰይጣን እንዲያውቀውም ጭምር ነው። ጥርጣሬ ስህተት አይደለም ስህተቱ እንዲያውም ሳይጠረጥሩ ሁሉን ማግበስበስ ነው። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ቢጠረጥሩ ኖሮ ያንን ሌላ ኢየሱስ፥ ሌላ መንፈስና ሌላ ወንጌል ባልተቀበሉም ነበር።

ምዕመናን በእልፍኛቸው ውስጥ ሆነው ቃሉን አብዝተው እንዲመረምሩና ስር እንዲሰዱ በጥሞና ጊዜያቸው ከጌታ ጋር እንዲጣበቁ ያስፈልጋል እንጂ አንዴ ወይም ሁለቴ በሚደረጉ ኮንፍራንሶች ላይ 'በረከት' የሚሉትን ነገር እንደ ቄስ ጠበል መረጨትን ሙያ ብሎ በመያዝ መንፈሳዊ ጉዞንና እርምጃን በነዚህ ጥቂት ቀናት ወይም ሣምንታት ብቻ ላይ መመስረት የዕድገት ምልክት አይደለም። ከመንፈሳዊ ሕፃንነት መላቀቅ ከእያንዳንዱ አማኝ የሚጠበቅ ባህርይ ነው። አገልጋዮችም ማኅበረ-ምዕመናን እንዲበስሉ እንጂ እንጭጮች እንደሆኑ እንዲኖሩ ማድረግ የለባቸውም። የሚሰጣቸውን ብቻ ሳይጠይቁ እንደ ሕፃን ከመጋት ደረጃ እንዲያሳልፉቸው ይጠበቅባቸዋል። ክርስቲያኖች የኮንፍራንስ ክርስቲያኖች ብቻ እንዳይሆኑ ማስልጠንም አለባቸው። ትልልቅ የጀማ ስብሰባዎችና የተጠቀጠቁ የቀናት ስብሰባዎች የመንፈሳዊ ሕይወታችን መስመር ማድመቂያና ማቆንጃ እንጂ የአቅጣጫውን የፊት ቀስት መቀያየሪያ መሆን የለባቸውም።

ለማጠቃለል የዚህ ነገር ማለትም የመውደቅ፥ በጌታ ቃልና በቤተ

ክርስቲያን ውስጥ በታሪክም ውስጥ የመኖሩ እውነትነት ግልጽ ነው። በዚህ ዘመን ከመቼውም ይልቅ ገንና እየተደረገ መሆኑና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ መንገድ እየተበላሸም መሰራቱ ግልጽ ነው። ሌላው ግልጽ ነገር ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ከሚሰራበት አካል ማለትም ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ይህ ነገር የሚደረግና የተለመደም መሆኑን ብዙ ሳንርቅ በአገራችን ከሚገኙ ቃልቻዎችና አዶከብሬዎች መገንዘብ እንችላለን። ሌላው ማለፍ የሌለብን ነገር ይህ ነገር ለክርስቲያን መንፈሳዊ ጉዞ አስፈላጊ ለመሆኑ ደግፎ የሚናገር አንድም ጥቅስ ያለመኖሩ ነው። ክርስቲያን ሊያነብ የተጠራው ቃሉን እንጂ የሰዎችን ልምምድ ባለመሆኑ ስለዚህ ነው ጠበቅ ያለ ጥንቃቄ የሚያሻው። ፈልጉ ያልተባልነውን ነገር እየፈለግን ስንተራመስ ማስመሰል የሚያውቀው ጠላት ሰይጣን አስመስሎ ሊያቀርብልን ይችላል፤ እኛም በየዋህነት ተቀብለን ቀዳዳ ልንከፍትለት እንችላለንና መጠንቀቅ ያሻል። 'ክርስቲያኖች ሆነን እንዴት ሰይጣን ሊያጠቃን ይደፍረናል እንዴትስ አምላካችን ይህ ሲሆን ይተወናል?' ይባል ይሆናል። መልሱ አጭር ነው መልካሙ እረኛ በቃሉ አማካይነት በሚያሰማራን ለምለም መስክ እንደ በጎች መሰማራት አለብን እንጂ እንደ ፍየሎች ያገኘነውን ቅጠል ሁሉ ለመቀነጣጠብና ለመሞከከር በየቋጥኙና በየጥሻው የምንቅበዘበዝ ልንሆን ደግሞ አምላካችን አልነገረንም።

## "የቀባኋቸውን አትዳስሱ"

ይህ ቃል በቀጥታ ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከብሉይ ኪዳን የተወሰደ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ከዓውዱ ሲወጣ እንደሚፈጥረው ያለ ችግር ይህም ቃል መፍጠሩ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ታይቷል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወይም የቃሉ አገልጋዮች ከወቀሳና ከተግሳጽ ለመዳን ሲፈልጉ እንደ ባንዲራ እያውለበለቡ የሚነሱበት ጥቅስ ነው ይህ ጥቅስ። ማስፈራሪያና መፍረጃ ከመደረግ አልፎ ደፍረው የጠየቁ አፋቸው እንዲታተምና ሁለተኛ እንዳይለመዳቸው በመደረግ ለቅጣት የሚዳረጉበትም ጊዜ አያሌ ነው። አገልጋዮች ፍጹም እንደሆኑ ከቶ እንደማይሳሳቱ ሁሉ ከመፈተንና ከመመርመር ነጻ መሆን የለባቸውም።

አንድ አገልጋይ አገልግሎቱ እየሰፋ፥ ነፍሳት እየዳኑ፥ የዳኑትም እየታነጹ፥ ጌታም በዚህ እየከበረ ሲመጣ ሰይጣንም በተራው የተሰራው ሁሉ በእርሱ በአገልጋዩ ብቻ የተሰራ አስመስሎ ሊያስታብየው ከሌላው ጊዜ ይልቅ ያመቻዋል። በአገልግሎት ውስጥ ስህተት ሊኖር ይችላል፤ ትልልቅ የተባሉ አገልጋዮችም እንከን ሊገኝባቸው ይችላል። አሮን ነበር የወርቅ ጥጃ የሰራው፥

ጴጥሮስ ክበር ጌታ ስለሞቱ ሲናገር 'ይህ አይሁንብህ' ያለው። አንዳንድ ጊዜ ትልልቅ ዳቦዎች ትልልቅ ሊጥ ይሆናሉ። አገልጋዮች የሚያጠፉት ጥፋት ለነርሱ ሳይታይ ለሌሎቹ ወለል ብሎ ሊታይ ይችላል። ስለዚህ ትህትናን መልበስና ለመታየትና ለመስተካከል ወይም ያንን ነገር ለምን እንደተደረገ የግፊትን ምክንያት ለመስጠት ዝግጁ መሆን ያሻል። አንዳንድ አገልጋዮች ግን በጭፍን፥ በእሻል ባይነትና በኩናኝነት ወንበራቸውንም እንደ ካህኑ ዔሊ ወድቀው እስኪሰበሩበት ላለመልቀቅ እየተንገታገቱ ይህን ቃል ይጠቅሱታል። የስልጣናቸው የክብር ዘብ አድርገው ያቆሙታል።

ይህ ቃል ስለ አገልጋዮች ይናገርና አይናገር እንደሆነ እስኪ እንመልከት። ጥቅሱ የሚገኘው በመዝ.105:14-15 ላይ ነው። እዚሁ መዝሙር ውስጥ ከ1-15 የሚገኙትን ጥቅሶች በ1ዜና 16:8-22 እናገኛለን። ይህ የኋለኛው ክፍል ዳዊት የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ይዞ በገባ ቀን የዘመሩት ነው። ይህ ክፍል በግልጽ እንደሚናገረው የእስራኤል ታሪክ በአጭሩ የተወሳበት ነው። እስራኤል እግዚአብሔር ህግንና ተስፋን የሰጠው ሕዝብ ነው። አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ የዚህ ሕዝብ መስራች አባቶች ናቸው። ይህ መዝሙር በቀጥታ የሚናገረው ስለ እስራኤል መስራች አባቶች እንጂ ስለ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አይደለም። አትንኩ ወይም አትዳስሱ ያለውም ይህን ምርጥ የሆነ ሕዝቡን ነው።

ግዑዛን ነገሮች ካልሆኑ በቀር በብሉይ ኪዳን በብዙ ቦታዎች 'የተቀቡ' ተብለው ሲጠሩ የምናያቸው ነገስታት ናቸው። (1ሳሙ.2:4፤ 10:1 ፤ 12:3-5፤ 16:13 ፤ 24:6-10 ፤ 26:9 ፥11፥16፥23፤ 2ሳሙ.1:14-16፤ 19:21 ፤ 1ነገ.1:39፤ 2ዜና.29:22) ንጉስ ከተቀባ በኋላ 'እግዚአብሔር የቀባው' ተብሎ ይጠራል። የብሉይ ኪዳን ካህናት ሲካኑም ይቀቡ ነበር። (ዘፀ.30:22-33) ነቢይ ሲቀባ ግን ከአንድ ቦታ በቀር አናይም ያም ነቢዩ ኤልሳዕ የተቀባበት ነው። (1ነገ.19:16) የብሉይ ኪዳን የነገስታት መቀባት ትርጉም ወደ አዲስ ኪዳን የሚጠቁም አመልካችነቱ ነው። ያም አንድ ቀን መሲህ ክርስቶስ መጥቶ በዳዊት ዙፋን የመቀመጡ ናፍቆት መግለጫ ነው። በግሪክ ቋንቋ ክርስቶስ ማለት 'የተቀባ' ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን 'የተቀባ' የሚባል ስም ያለው ጌታ ብቻ ነው። በተቀረ ከክርስቶስ የተነሳና መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ከመኖሩ የተነሳ አማኞች ሁሉ የተቀቡ ናቸው።

በአዲስ ኪዳን ቅብዓት የተባለው አሳብ 30 ጊዜያት ሲጠቀስ ከነዚህም 11ዱ "ዘይት" ተሰኝተዋል። 19ኙ ደግሞ በግሪክ ቋንቋ ወደ ስድስት የተለያዩ ቃላትን በመጠቀም "መቀባት" እና "ቅባት" የሚለው ቃል የተጠቀሰባቸው ናቸው። ከእነዚህ ከአስራ ዘጠኙ አስራ ሁለቱ በአካል ላይ የሚቀቡትን ወይም

የሚፈስስን አንድ ወይም ሌላ ዓይነት ንጥረ-ነገር ሲያመለክቱ ሰባቱ ግን ክርስቶስም ሆነ አማኞች የተቀበሉበትን ሁኔታ ያመለክታሉ። እነዚህ ሰባት ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው፤ ሉቃ.4:18፤ ሐዋ.4:27፤ ሐዋ.10:38፤ 2ቆሮ.1:21፤ ዕብ.1:9፤ 1ዮሐ.2:20፤ 1ዮሐ.2:27።

በአዲስ ኪዳን የተወሰኑ አገልጋዮች ለተለየ አገልግሎት ተብሎ ሲቀቡና ሲለዩ በፍጹም አንመለከትም። ቃሉ ግን ስዕላዊ በሆነ መንገድ ሰማያዊ ሹመትን በተለይም የክርስቶስን መቀባት ያመለክታል። (ሉቃ.4:18፤ ሐዋ.4:27፤ 10:38 ፤ ዕብ.1:9) በ2ቆሮ.1:21 ጳውሎስ ራሱና አማኞች ሁሉ በክርስቶስ አማካይነት በእግዚአብሔር እንደተቀቡ ይናገራል። በ1ዮሃ.2:20 እና27 ደግሞ አማኞች ሁሉ ቅባትን እንደተቀበሉ ተጽፏል። እዚህ ቦታ ቅባት ተብሎ የተጠቀሰው የራሱ የመንፈስ ቅዱስ ኅልውና ነው። ስለዚህ ማንም ዳግም የተወለደ አማኝ በአዲስ ኪዳን ቋንቋ የተቀባ ነው ማለት ነው።ይህ መቀባት ደግሞ ከሆነ ልዩ አገልግሎት ጋር የተያያዘ የሹመት መግለጫ ሳይሆን ትክክለኛን ትምህርት ትክክለኛ ካልሆነው ለይቶ ከማወቅ ማስተዋል ጋር የተዳበለ አሳብ ነው። ስለዚህ "እገሌ የተቀባ አገልጋይ ነው"ተብሎ ሲነገር ምንም እንኳ በዘልማድም ቢሆን ምን እየተባለ እንደሆነ መስተዋል አለበት። እንዲህ ሲባል ለአድናቆትና በየዋህነት ለጥሩ ነገር መሆኑ ግልጽ ነው ይሁን እንጂ "እገሌ የተቀባ ነው"ካልን "እገሌ ደግሞ የተቀባ አይደለም"ማለታችን መሆኑ መዘንጋት የለበትም።ደግሞም መቀባት የሚለውን ቃል አተረጓጎማችን አሻሚና አወዛጋቢ ሊሆን መቻሉ የማይታለፍ እውነት ነው።

ወደተነሳንበት አሳብ ለመመለስ "አትዳስሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አካላዊ ጉስቁልናና ቅጣትን እንጂ ማንም አዲስ ነገር ተገለጠልኝ ባይ አስተማሪና እራሱን በራሱ እጅ የቀባ ነቢይ ነኝ ባይ የሚናገረው ነገር በእርግጥ ከጌታ ይሁን ወይም አይሁን ለማረጋገጥ ቃሉን ተደግፎ መጠየቅን አያመለክትም። ማንም ሰው ዛሬ ተአምር ቢሰራ "የተቀባ ነው አትናገሩት" ካልን ነገ ሐሰተኛው ክርስቶስ መጥቶ የሚያምኑትን እንኳ እስኪያስት የሚያደርሰውን ተአምራት የማንቀበልበት ምን ምክንያት ይኖረናል? የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሚታወቁበት ዋና ባህርይ ንፁሕ ኑሯቸውና ያልተበረዘ ትምህርታቸው ነው። ይህንን መለኪያ የማያልፈውን ማንንም ሰው የምንቀበልበት ምክንያት ወይም የማንጠይቅበት ፍርሃት ሊኖረን በፍጹም አይገባም ። ሃንክ የተባለ ሰው እንዲህ ብሎ ጽፏል፥

> የማንም ሰው በተለይም የትላልቅ መሪዎች
> ትምህርቶችም ሆኑ ልምምዶች ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ግምገማ
> የሚያመልጡ መሆን የለባቸውም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ

እውነት ስልጣንና ተጠያቂነት እጅ ለእጅ የተያያዙ ናቸው።(ለምሳሌ ሉቃ.12:48) የአንድ ሰው ኃላፊነት ባደገ ልክ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ፊት ያለው ተጠያቂነትም በዚያው ልክ ነው።[9]

መሰረተ ቢስ የሆነ ወቀሳ ይዘው የሚነሱና በቅናት የአንድን ሰው ትምህርት በማክፋፋት ስሙን የሚያስጎድፉ ሰዎች ሊኖሩ መቻላቸው እውን ነው። እንዲህ ያለው ጥያቄ ከተነሳ አስተማሪው ጠያቂው መሳሳቱን ከቃሉ በመጥቀስና በየውኃት መንፈስ ማመልከትና ማስረዳት መቻል ይገባዋል። ነገር ግን እውነተኛ የሆነን ነገር ይዘው ለሚያርሙት ደግሞ ፈቃደኛና እንዲያውም እግዚአብሔርንና እነርሱንም አመስጋኝም ሆነ ለመቀበል መጨከን አለበት።

ሰዎችን ወይም አገልጋዮችን ስንል ሰዎችን ስለ ሰውነታቸው ማለትም ሰዎች ስለሆኑ ብቻ መጠራጠር ሳይሆን የሚያደርጉትን ነገርና የሚለማመዱትንና የሚያለማምዱትን ነገር ኮስተር ብሎ መመልከት ነው። አንዳንዴ በጉባዔ ውስጥ አንድ ሰው ድምጹን ከፍ አድርጎ በሚታወቅም ቋንቋ ይሁን በልሳን ሲናገር አድማጭ ሁሉ አንገቱን ቀልሶ በፍርሃት መስማትና መስማማት እንዳለበት ተደርጎ ይወሰዳል። ልክ እግዚአብሔር በዚያ ሰዓት በቀጥታ እየተናገረ እንደሆነና ማንም ሰው ይህን መልዕክት ሳይጠራጠርና ሳይጠይቅ መቀበል እንዳለበት ይነገራል። አንዳንዶች የተጻፈው ቃል ሲነበብ ለሚነበበው ቃል ከሚሰጡት አክብሮት ይልቅ ለዚህ ለሚነገረው የሚሰጡት ይበልጣል። ለምን ሲባል ከተጻፈው ይልቅ ያ ቃል እንደተቀባ ተደርጎ ስለሚገመትም ነው። ይህ የሰው ልማድ እንጂ የቃሉ ትምህርት አይደለም።

ነቢያት በጉባዔ በሚናገሩበት ጊዜ የሚናገሩትን ነገር የእግዚአብሔር ሕዝብ አሚን ብሎ መቀበል ሳይሆን መመርመር እንዳለበት 1ቆሮ.14:29 "ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ ሌሎችም ይለዩአቸው" ብሎ ይነግረናል። 'ይለዩአቸው' ሲል መለየት ማለት የሚነገረውን መልእክት ይመዝኑት ማለት ነው። መናፍስትን መለየትም ከስጦታዎች አንዱ ነው። መናፍስትን መለየት ማለት አንድ የተነገረ መልዕክት ከእግዚአብሔር፥ ከሰው ወይም ከአጋንንት አሳብ መሆኑን መለየትና ማወቅ ማለት ነው። የተነገሩ ነገሮችን ሁሉ 'እግዚአብሔር ተናገረ ወይም መንፈስ ቅዱስ ተናገረ' ብሎ በየዋህነት መቀበልን ቃሉ አይደግፍም። ሃሰተኛ ነቢያት ከቀድሞ ጀምሮ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል እንደነበሩ በዘመናችንም የማይኖሩበት ምክንያት የለም። እንዲያውም በዘመን መጨረሻ ያለን ነንና እንደሚበዙ ተጽፎልናል። በብሉይ ኪዳን እንዲህ ያሉትን ነቢያት የእግዚአብሔር የሆኑቱ መፍራት እንደሌለባቸው ተጽፏል። (ዘዳ.18:22) በዘዳ.13 በስፋት እንደምናየው ደግሞ ይህን መሳይ የውሸት ነቢያት የተግባራቸው ውጤት

ማስካድ ስለሆነ መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ተወግረውም ይገደሉ ነበር።

የእግዚአብሔር ሰዎች ነገሮችን እንዴት በቀላሉ የሚያምኑና የሚቀበሉ መሆናቸው በጣም ያስገርማል። የአንዳንድ አታላዮችን ማታለል ሳይጠይቁ ለመቀበል መቻኮላቸው ለአደጋ እንደሚያጋልጣቸው ግልጽ ነው። በመጨረሻው ዘመን ሃሰተኛው ክርስቶስ መጥቶ ድንቅ ነገር ሲያደርግ የሚያምኑት እንኳ ይስቱለት ይሆናል። ምልክቶችን ብቻ የሚያዩ ይደናቀፋሉ፥ ሰውየውንም የሚያዩና የሚያስተውሉ ግን ጥበበኞች ናቸው። ድንቅ ነገር በእጃቸው የተደረገን ሁሉ የተቀቡ ናቸው ብሎ መወናበድ የዋህነት ነው። ቃሉም እንዳንታለል አበክሮ ያስተምረናል። (ማቴ.24:4፤ ኤፌ.4:14) በማቴ.12:31-32 እንደተጻፈው መንፈስ ቅዱስ የሰራውን እግዚአብሔር ያደረገውን የሰይጣን ነው ብሎ መፍረድ ኃጢአት እንደሆነ ሁሉ በዚያው ልክ ደግሞ የስጋንና የሰይጣንን ነገር የመንፈስ ቅዱስ ነው ማለትም ኃጢአት መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

ይህ ካልሆነ የስህተት አስተማሪዎችን የመግለጡ ኃላፊነት እንደምን ሊደረግ ነው? (ሮሚ.16:17-18፤ 1ጢሞ.1:3-4፤ 2ጢሞ.4:2፤ ቲቶ.1:9፥ 3:10-11) ቅዱስ ቃሉ አበክሮ የሚያስረዳን የተሳሳቱ መታረም እንደሚገባቸው ነው። 'እግዚአብሔር ቀብቶኛልና አትንካኝ' የሚሉቱ እንዲያውም የበለጠ መፈተሽ ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም በእርግጥ ስህተተኛ መሆናቸውን ያወቁት ይህን የቃሉን መሸፈኛ ወስደው ስለሚጎናጸፉትና ከተጠያቂነ ነፃ መሆን ስለሚፈልጉ መግለጥ ስለሚገባቸው በየዋህነት ተሳስተው የሚሳሳቱትም ከስህተታቸውም ሆነ ከማሳሳታቸው እንዲታረሙና እንዲመለሱ ነው። ትክክለኛ አገልግሎት የሚያገለግሉት ቢጠየቁም ቅሬታ እንደማይሰማቸው ግልጽ ነው። የዕቃ መመዘኛ ሚዛኖችን የወሰድን እንደሆነ በጊዜ ብዛት ሊበላሹና ትክክል ላይሆኑ ይችላሉ በአገራችን የደረጃዎች መዳቢ ድርጅት የሚባለው መስሪያ ቤት ይህን ችግር ለማስተካከል የሚያደርገው ነገር አለ፤ ያም አንድ ትክክል የሆነ መመዘኛ አለው ሚዛኖች ሁሉ በየዓመቱ በዚያ መመዘኛ ተፈትነው ያን ፈተና ማለፍ አለባቸው። ክርስቲያን የተመደበ ሁሉ የማይለዋወጥ ደረጃ ወይም መመዘኛ አለው ማንም የሚሰጠው ትምህርት ሁሉ በዚያ ደረጃ መለካት አለበት። ያ ደረጃ ወይም መለኪያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፤ ይህም ሲባል አንድ ጥቅስ ወይም አንድ የምንባብ ክፍል ብቻ ማለት ሳይሆን ሙሉው የእግዚአብሔር አሳብ በቃሉ እንደተገለጠ ማለት ነው።

ሰዎች ወይም አገልጋዮች 'የእግዚአብሔር ዕቃዎች'፥ 'የተቀቡ'፥ 'ኃይል የለበሱ' ወዘተ. እየተባሉ መለስተኛ አማልክት እየሆኑ የመጡበትም ጊዜ ነው፤ ይህ ጊዜ። በምዕራቡ ዓለም ቋንቋ (Personality Cult) ይባላል። አምልኮተ-

ለቃሉም ጊዜ ያለመስጠት ነው።

እንዲህ ያሉ መሪዎች በተወሰኑ ብቻ ሳይሆን በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ሊኖሩ እንደሚችሉ ግልጥ ነው ቢሆንም "ከሌሎች የተሻልን ነን፥ ከሌሎቹ ይልቅ የቃሉ መገለጥ አለን ...." በሚሉት ዘንድ ደግሞ ይብሳል። ይህ ማለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አስተማሪዎችን፥ ሰባኪዎችን፥ መጋቢዎችንና ሌሎችም የቃሉ አገልጋዮችን አንመናቸው ማለት አይደለም የሚገባቸውን ክብርና በቃሉም መሰረት ሊሰጣቸው የሚገባቸውን አክብሮት ልንነፍጋቸው ከቶ አይገባም። ቃሉ በብዙ ቦታዎች (ለምሳሌ 1ተሰ.5:12-13 ዕብ.13:17) አገልጋዮቻችንን ማወቅ ማክበር መታዘዝና መገዛት እንደሚገባን ያስተምረናል። እንኳን እግዚአብሔር በቤቱ ውስጥ ላኖራቸው አገልጋዮች ይቅርና ሮሜ.13 እንደሚለው ክርስቲያን ለዓለማዊ ባለስልጣኖች እንኳ መገዛት አለበት። እንግዲህ እኒህን አገልጋዮች እንውደዳቸው ነገር ግን እናምልካቸው። አንዳንዶቹ ይህን ጥቅስ ማስፈራሪያ የሚያደርጉት ልክ አባይ ጠንቋዮችና ቃልቻዎች እኩይ ስራቸውን ለመሸፈን በነርሱም ላይ የሚደረገውን ሐሜትና ነቀፋ ውቃቢያቸው የሚበቀል መሆኑን በሚያስረዱበት መንገድ ነው። ከ1ጢሞ.5:19 ቤተ ክርስቲያን መሪ ላይ ማንም በዘፈቀደ ጣቱን መቀሰርና ክስ መመስረት እንደማይኖርበት እንረዳለን። ነገር ግን 2ወይም3 ምስክሮች ካልኖሩ በቀር በሽማግሌ ላይ የሚሰነዘር ክስ አትቀበል ሲል 2 ወይም 3 ከኖሩ አትቀበል ማለቱም ያለመሆኑን ልንረዳ ይገባል።

ቀደም ሲል በመጠኑ እንደተመለከትነው ዛሬ ይህ "ቅባት" ወይም "መቀባት" የተሰኘው ቃል በሁለት አቅጣጫዎች በስህተት እየተለጠጠ በቤተ ክርስቲያን ላይ ክፉ አደጋ እየፈጠረ ነው። እነዚህ ሁለት አቅጣጫዎች አንደኛው ያለ ቤተክርስቲያን ጠሪነትና የጌታም ጥሪ ምስክርነት ባለስልጣን መሆን ወይም መደረግ ሲሆን ሁለተኛው አገልግሎት ውስጥ እውነተኛ የሚመስል ውጤት እንዲሁም ጥቂት ተከታዮችን ማፍራትን በማስመዝገብ አለሁ ባይ መሆን ናቸው። ዛሬ በአንዳንድ አካባቢዎች ይህ አዝማሚያ መስመር እየሳተና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሙንም እየተገፈፈ ይገኛል። በአንዳንድ ሰዎች ዘንድም መሿሿሚያ እየተደረገ መቀባባትና እራሳቸው የተቀባቡትን "የጌታ ቅባት ባንተ ላይ ነው፥ ጌታ ቀብቶሃል" መባባል እየተሰማ መጥቷል። በትንንሽ ቢልቃጦች ዘይት በኪስ እየያዙ መጓዝና ምትሃታዊ የሚመስሉ ነገሮችን መስራት እየታየ መጥቷል።

የአዲስ ኪዳን መቀባት ምን እንደሆነ ቀደም ሲል በአጭሩ አይተን ነበር፤ እስኪ ጥቂት እናብራራው። በብሉይ ኪዳን ዕቃዎች ይቀቡ ነበር፤ በአዲስ ኪዳን ይህን አናይም። ወደ ሰዎቹ ከተመለስን ነቢይ አንዴ ብቻ እንደተቀባ ሲጻፍ

ክህናትና ነገስታት በተለያዩ ቦታዎች መቀባታቸው ተወስቷል። እኛ የአዲስ ኪዳን አማኞች የተለየን ባለ ቅባት ካህናት ወይም የተለየን የተቀቡ ነገስታት መሆናችን የተነገረን አንድም ጥቅስ የለም። ጌታን የተቀበልን ሁላችን ካህናት ነን (1ጴጥ.2:9) ደግሞም ልጆቹ ከሆንን ሁላችንም የመንግስቱ ወራሾች ነን። የተለየ "የተቀባ" የሚባል የክርስቲያን መደብ ከቶውኑ የለም።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ "ቅባት"፥ "መቀባት"፥ እና "ዘይት" የተሰኙት ቃላት 30 ጊዜያት ያህል ተጽፈዋል። "መቀባት" የሚለው ቃል በሰውነት ላይ መልካም ሽታ ወይም መዓዛ ያለውን ፈሳሽ በማፍሰስ ማሸትን ወይም ማውዛትን ያመለክታል። "ዘይት" የሚለው ቃል ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል የወይራ ዘይትን ማለቱ ነው።

መቀባት የሚለው ግስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በአምስት የተለያዩ የግሪክ ቃላት ተጠቅሷል። እነዚህም ጥቅሶች፤

| | | |
|---|---|---|
| ማቴ.6:17 | ማር.6:13 | ማር.14:8 |
| ማር.16:1 | ሉቃ.4:18 | ሉቃ.7:38 |
| ሉቃ.7:46 | ዮሐ.9:6 | ዮሐ.9:11 |
| ዮሐ.11:2 | ዮሐ.12:3 | ሐዋ.4:27 |
| ሐዋ.10:38 | 2ቆሮ.1:21 | ዕብ.1:9 |
| ያዕ.5:14 | ራዕ.3:18 | ዕብ.1:9 |

ቅባት "ክሪዝማ" በተሰኘ የግሪክ ቃል ተገልጧል። ይህ ቃል ካሪዝማ ከተሰኘው ቀደም ሲል ከተመለከትነው ቃል የተለየ ነው። (ክርስቶስ የሚለው ቃልም ከዚህ ክሪዝማ ከሚለው ቃል የመነጨና የተቀባ ማለት ነው።) ይህ በዚህ ቦታ ቅባት የተባለው ቃል አማኞች ሁሉ የተቀበሉትን መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ነው። ይህ ቃል ሁለት ቦታዎች የተጠቀሰ ሲሆን እነዚህም 1ዮሐ.2:20 እና 27 ናቸው።

ዘይት "ኢላዮን" ማለት በግሪክ የወይራ ዘይት ማለት ሆኖ ለተለያዩ ግልጋሎቶች የሚውል ነው። እነዚህ ጥቅሶች የተጠቀሱባቸው ቦታዎች ከታች

የተዘረዘሩት ናቸው።

| | | |
|---|---|---|
| ማቴ.25:3 | ማቴ.25:4 | ማቴ.25:8 |
| ማር.6:13 | ሉቃ.7:40 | ሉቃ.10:34 |
| ሉቃ.16:6 | ዕብ.1:9 | ያዕ.5:14 |
| ራዕ.6:6 | ራዕ.18:13 | |

ይህ ቃል ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ በሰዎች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በአገልግሎቶች ለምሳሌ ስብከት፥ መዝሙር፥ ድምጽ ወዘተ. እና በመሳሰሉት ላይ እየተቀጸለ አማኞችን እያደናገረ መጥቷል። "የእገሌ ስብከት የተቀባ ነው"፥ "በዚያ መዝሙር ውስጥ ያለው ቅባት ልዩ ነው" የሚሉ የተለምዶ አነጋገሮች በዝተው ይሰማሉ። በዚህ "ቅባት" በተሰኘ ርዕስ ላይ መሠረታቸው መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን ሰብዓዊ ልምምድ ብቻ የሆኑ ብዙ ስብከቶች ተሰብከዋል። በእርግጥ ጌታ አገልግሉ ብሎ የጠራቸው አገልጋዮች የመኖራቸውን ያህል ሳገልግል ብለው የተነሱም በብዛት መኖራቸው የማይካድ ነው። እነዚህ አገልጋዮች ፍሬያማ ባይሆኑ ማስገረም የለበትም ከሆነ ደግሞ ለዚህ አባባል ወይም ለነዚህ አገልጋዮች የምንሰጠው የመግለጫ ቃል "ቅባት" ወይም "መቀባት" የሚለው መሆን የለበትም። ሌላ ማብራሪያ ካስፈለገ ሌላ ቃል እንጠቀም እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳችን የማይለንን አዲስ ትምህርት ፈጥሮ ሰዎችን ማደናገር ተገቢ አይደለም። ስለዚህ "ቅባት" "መቀባት" ወይም "የተቀባ" የሚሉትን ቃላት በምንናገርበት ጊዜ ምን እያልን መሆናችንን ማጤን ተገቢ ነው።

## ፈደልና መንፈስ፥ ቃልና ኃይል?

ይህ የፈደልና የመንፈስ ነገር በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ እንደመለያ ተደርጎ የሚጠቀስ ነገር ሆኖአል። አንዳንድ ሰባኪዎች የሚናገሩት ነገር ኃይልና መንፈስ የሌሎች ደግሞ ደረቅ ቃልና የሚገድል ፈደል እንደሆነ እየተደረገ ግድግዳ ይገነባበታል። የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት የሚያስተምሩ አገልጋዮች በሌሎች ሰዎች ልምምድ ሲታይ መንፈስና ኃይል የሚባለው ነገር የሌላቸው እየተደረጉ ይጥላሉበታል - ግርፕ አጥንት፥ ደረቅ እንጨት፥

የሚንኳኳ ቆርቆሮ ወዘተ. እየተባሉ በግልጽ የተነቀፉም አሉ።

ፊደልና መንፈስ ተቃራኒ ነገሮች ናቸው? ቃልና ኃይልስ ተቃራኒ ነገሮች ናቸው? መጽሐፍ ቅዱስስ ሰዎች እንደሚሉት ሁሉ እነዚህ ነገሮች ተቃራኒ መሆናቸውን ያስተምራል? በሮሜ.2:27 እና 29 ላይ 'የሕግ መጽሐፍ' እና 'መጽሐፍ' ተብለው የተጠቀሱት ቃላት በሌላ ቦታ ፊደል የተባሉት ናቸው። ይህ ክፍል በስፋቱ ስናየው ስለ አይሁዳዊ ብልጫ ይናገራል። እዚህ ፊደል ወይም መጽሐፍ የሚለው ቃል የተጠቀሰው የእውነተኛ አይሁዳዊ መለኪያ ከህጉም ባሻገር የልቡ ጉዳይ መሆኑን ነው። ሮሜ.7:6 መንፈስና ፊደል ጎን ለጎን የተጠቀሱበት ቦታ ሲሆን ፊደልም መንፈስም ከኑሮ ጋር ነው የተጻፉት። በሮሜ.6 ጳውሎስ አማኝ ከክርስቶስ ጋር መሞቱን፥ መቀበሩንና መነሳቱን ስዕላዊና ገላጭ በሆነ መንገድ ካሳየ በኋላ በምዕራፍ 7 አንዲት ሴት ለሁለት ባሎች በአንድ ጊዜ ሚስት እንደማትሆን ሁሉ ክርስቲያንም ለሁለት ስርዓቶች ማለትም ለአሮጌው የፊደል ሕግ (የብሉይ ኪዳን የሕግ ስርዓት) እና ለአዲሱ የመንፈስ ሕግ (የአዲስ ኪዳን የጸጋ ስርዓት) በአንድ ጊዜ ሊገዛ እንደማይችል መናገሩ ነው። እዚህ ስፍራ አሮጌው የፊደል ኑሮ የተባለው በጠቅላላው የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት በመጠበቅ ሊገኝ የሚሞከረው ደኅንነት ነው እንጂ የአንድ ሰባኪን ስብከት ወይም ትምህርት አይደለም።

ለዚህ ዓይነቱ ክስ ተደጋግሞ የሚጠቀሰው 2ቆሮ.3:6 ደግሞ እንዲህ ይላል፤ "እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል።" ከላይ በቁጥር 3 የስጋና የድንጋይ ጽላት እንዲሁም መንፈስና ቀለም ጎን ለጎን እየተደረጉ ተጠቅሰዋል። ከቁጥር 7 ጀምሮ ደግሞ እስከ ምዕራፉ መጨረሻ ስናነብ አሁንም ሙሴን፥ ሕግን፥ ጽላትን እናገኛለን። በአንፃሩ ደግሞ ከሕግ ወደ ጸጋ ከሙሴም ወደ ክርስቶስ ዘወር ስንል መንፈስ ከሆነ ጌታ የሚሆን አርነትን እናያለን። እንግዲህ እዚህም መንፈስና ፊደል የሚባሉት የብሉይና የአዲስን ስርዓትና አገልግሎቶች ክብር ልዩነት የሚያሳይ ነው። የአዲስ ኪዳን ትምህርት በሙሉ የመንፈስ ትምህርት ነው፥ የአዲስ ኪዳን አገልጋዮችም በሙሉ የፊደል አገልጋዮች ተብለው ሊጠሩ ከቶ አይገባም። ይሁን እንጂ ማንም ሰባኪና አስተማሪ የሆነ የቃሉ አገልጋይ ትምህርቱን ወይም ስብከቱን ለማዘጋጀት ከሚጸልይበት ጊዜ አንስቶ ለምዕመናን እስከሚያሳልፍ ድረስ በመንፈስ ቅዱስ መታመን አለበት። ደግሞም ቃሉን እንደ እግዚአብሔር ቃል መመገብ እንጂ እንደ ዜና አንባቢ ብቻ ማስተላለፍ የለበትም። ከአገልጋዩ ሕይወትና ከዝግጅቱ መበላሸት የተነሳ ይህ ሕያው ቃል በሙተፎ መንገድ ሊቀርብ እንደሚችል መዘንጋት የለበትም።

ቃልና ኃይልስ? በ1ቆሮ.4:20 ላይ ጳውሎስ የእግዚአብሔር መንግስት በኃይል እንጂ በቃል እንዳልሆነች ይናገራል። እዚህ ስፍራ ቃል ተብሎ የተጻፈው በአዲስ ኪዳን በአብዛኛው ቃል (ወይም ሎጎስ) ተብሎ የተጠቀሰው ነው። በዮሐ.1:1 ጌታ ራሱ የተጠራበት መጠሪያ ይህ ቃል ነው። በ1ቆሮ.1:18 ቃሉ ማለትም የመስቀሉ ቃል ኃይል መሆኑ ተጽፏል። በ1ቆሮ.4:20 ላይ ጳውሎስ የጠቀሰው ቃልና ኃይል የተለያዩና ምንም አንድነት የሌላቸው መሆኑን ለማሳየት ሳይሆን በቆሮንቶስ የሚገኙ ከፋፋይና ትዕቢተኞች አስተማሪዎች የሚያስተምሩት ትምህርት የእግዚአብሔር አሳብ ሳይሆን ወሬ ብቻ መሆኑን መናገሩ ነው። በ1ቆሮ.2:1-13 ጳውሎስ ቃሉን ሲገልጥ በሰው ጥበብ ሳይሆን መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ እንደሆነ ገልጧል። ሊገልጥ የተጋደለውም ለዘመናት ተሰውሮ የኖረው ጥበብ ሌላ ሳይሆን ክርስቶስ ነው።

ደግሞም ኃይል ያለው በቃሉ አማካይነትና ውስጥ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል በሌለበት የእግዚአብሔር ኃይል የለም፥ ሊኖርም አይችልም። ሰዎችን የሚያድን፥ የሚለውጥ፥ የሚፈውስ፥ ኃይል ያለው በሰዎች ቃል ወይም ድምጽ ውስጥ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ነው። ዕብ.4:12እንደሚነግረን ቃሉ ሕያው ነው። ይህ ማለት ሕይወት አለው ማለት ነው፤ ሕይወት ካለው ጉልበትም አለው። ጉልበት ስላለው ነው ቃሉ ያሸነፈን፥ አሁንም የሚያሸንፈን። እንዲህ ያለ ኃይል ያለው ቃል ማንም ፈላስፋ ወይም የኃይማኖትም ሆነ የሌላ ነገር መሪ ኖሮት አያውቅም። የእግዚአብሔር ቃልና ኃይል የማይቆራኙና አንዱ አንዱን ገፍቶ የሚጥል ተቃራኒ ነገሮች አይደሉም። በማቴ.22:29 ጻሕፍትና ፈሪሳውያን የተወቀሱት ቃሉን ስላላወቁ ሳይሆን መጻሕፍትንና ኃይሉን ስላላስተዋሉ ነበር። የወንጌሉ ቃል ለማዳን የሚሆን የእግዚአብሔር ኃይል ነው። (ሮሜ.1:16) አሁንም መሳት የሌለብን ነገር መንፈስ ቅዱስ ሙሉ መለኮት የሆነ አምላክ እንጂ ኃይል አይደለም። አንዳንድ የስህተት ትምህርት ተከታዮች የሆኑ ሰዎች (ለምሳሌ የይሆዋ ምስክሮች) መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ላይ የሆነ ተጽዕኖ በማሳደር አንድ ነገር እንዲሰሩ የሚያደርግ ኃይል እንጂ አምላክ መሆኑን ይክዳሉ። መንፈስ ቅዱስ ኃይል ያለው አምላክ እንጂ እራሱ 'ኃይል ብቻ' የሆነ ነገር አይደለም። አማኞች በቅድስና እንዲኖሩ፥ ፈተናን ለማሸነፍ ወይም እንዲያገለግሉ ብርታትን የሚሰጥ የብርታት ምንጭ ነው እንጂ መንፈስ ቅዱስ እንደ ኤሌክትሪክ እንደ እንፋሎት ወይም እንደ ቤንዚን ያለ ጉልበት አይደለም። መንፈስ ቅዱስን እንደዚያ ማለትም እንደ ኃይል ብቻ አድርጎ ማሰብ ከስህተት አስተማሪዎች የተቀሰመ አደገኛ ስህተት ነው።

በ1ተሰ.1:5 ወንጌል በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ

በቃል ብቻ ወደ ተሰሎንቄ እንዳልደረሰ ተጽፏል። ይህ አገላለጽ ወንጌል የደረሰበትን ሁኔታ የሚያሳይ ነው። የእግዚአብሔር ቃል በሚሰበክበት ጊዜና ቦታ መንፈስ ቅዱስ የመለወጥና የማረጋገጥ ስራን ይሰራል። ማለትም የሚያምኑት የተለወጠ ሕይወት እንዲኖራቸው ያደርጋል፥ መዳናቸውንም ያረጋግጥላቸዋል። ሰዎችንም የሚለውጠው ኃይል ምንጭ መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ ሰዎች በራሳቸው ኃይል ራሳቸውን ሊለውጡ አይችሉም።

የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር መንፈስ ወይም እስትንፋስ ያለበት መሆኑን መዘንጋት የለብንም። 2ጢሞ.3:16-17 እንደሚነግረን 'የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ' ሲል ይህንን እውነት ነው። በዮሐ.6:63 ጌታ ተመሳሳይ እውነት ሲናገር 'እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው' ብሏል። እርጥብና ደረቅ ቃል ብሎ ነገር የለም። ቃል ቃል ነው፤ እግዚአብሔርም ሁሌም ከቃሉ ኋላ ይተጋል። ችግሩ ያለው ከተናጋሪዎች ወይም ከሰሚዎች ነው። የተናጋሪዎች የተቀደሰና የተሰጠ ሕይወት ከቃሉ አገልግሎት ተለይቶ መታየት የለበትም። ከዚህ ባላነሰ መታለፍ የሌለበት የሰሚዎች ወይም የአድማጮች የራሳቸው ሕይወት ነው። ሰዎች የደረቁ ሊሆኑ ይችላሉ፥ ቃሉ ግን የደረቁትን የሚያቃጥል እሳት ነው እንጂ ደረቅ አይደለም፥ አይሆንምም፥ ሆኖም አያውቅም። ስለዚህ ፊደል፥ ቃል፥ መንፈስ፥ ኃይል ስንል ምን እያልን እንደሆነ አበክረን ልናስተውል እነዚህን ቃላት ከየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደወሰድንና የወሰድነውም ዐውደ ንባብ ስለምን እንደሚናገርም ማወቅ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። በዚህም የዘመናችንን ቤተ ክርስቲያን እያወከ ካለው ከቃሉ በተመዘዘ አንድ ጥቅስ ላይ ትምህርትን መስርቶ ተሳስቶ ከማሳሳት ልንጠበቅ እንችላለን።

## የመገለጥና የጭንቅላት ዕውቀት

የዚህ ዘመን ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ከተጀመረበት ከዚህ ምዕት ዓመት መግቢያ ጀምሮ አዕምሮን መጠቀምና እየተደረጉ ያሉ ነገሮችን በአዕምሮ መመርመር ኢ-መንፈሳዊ ተደርገው እንዲታዩ በግልጽም በተዘዋዋሪም ተስተምረዋል። "የምትሰማውን ሁሉ አምነህ መቀበል አለብህ፥ ተዓማኒ ያልሆኑ ምስክርነቶችን ስትሰማ ሳትጠይቅና ሳታረጋግጥ ተቀብለህ 'ጌታ ይመስገን' ማለት አለብህ፥ ተአምራት ከተደረጉ ምንጩን ወይም በዚያ ጊዜ የሚያገለግለውን አገልጋይ ማንነት ሳትጠራጠር በደፈናው ተቀብለህ መደነቅ አለብህ።" የሚባል ይመስላል። ለምን? ቢባል 'በአዕምሮ ልትደርስበት

አትችልም! ስለዚህ ይህን የምታስብበትን ጭንቅላትህን ዘግተህ፥ ጆሮህን ከጭንቅላትህ አውርደህ አደረትህ ላይ አድርገህ የምትሰማውን በቀጥታ ወደ ልብህ እንዲገባና ለተባለው ሁሉ አሜን እያልክ መቀበል አለብህ" የሚል ይመስላል። መንፈሳዊ የሆነው ነገር ሁሉ አዕምሯዊ የሆነውን ሁሉ ካላለፈ መንፈሳዊ እንዳልሆነ ማሰብ ትክክለኛ አመለካከት አይደለም። በእርግጥ መንፈሳዊ የሆነውን ነገር በጥሬ አዕምሮ ብቻ ልንረዳው አንችልም። ይህ ማለት ግን አዕምሮ የሚያስበው ሁሉ መንፈሳዊ አይደለም ማለት አይደለም። በእንደዚህ ያለ ስህተት የሚወናበዱ ሰዎች የጸጋ ስጦታዎችን ሲለማመዱ ለምሳሌ አንድ ሰው ትንቢት ሲናገር ወይም በልሳን ሲናገር አዕምሮን እንደ ኤሌክትሪክ መብራት አጥፍቶ ነገሩ ሲያልቅ ወይም ሲያበቃ መልሶ እንደ ማብራት በመካከል ባለው ጊዜ ግን 'ለመንፈስ ቅዱስ ባዶ እንደመሆን' ይቆጥሩታል። ይህን የተማሩ አንዳንዶች ወደ ሰመመን፥ ኅሊናን ወደ መሳት፥ ከአዕምሮ ውጪ ወደመሆን ወዳለመኖር ወደመጠጋትና በተመስጦ ውስጥም ወደ መጥፋት ይቀርባሉ። ለምሳሌ "በመንፈስ መገንደስ" በሚባለው ርዕስ ሥር የተጠቀሰችው በ1920ዎቹ ውስጥ ታገለግል የነበረችው ማርያ ውድ ወርዝ-ኤተር ይህን መሰሉን የመመሰጥ እንቅስቃሴ ታራምድ ስለነበር 'ተመሳጪ ወንጌላዊት' እስከመባል መድረሷ ተዘግቧል። ተመስጦ ውስጥ በመግባት ረጅም ጊዜ እንደምትቆይም ይነገርላታል። አንዴ እንዲያውም እየሰበከች ሳለች ለሦስት ቀናት እንደ ሐውልት ደርቃ መሰንበቷም ተጽፏል።[10]

ኬንት ሄግን የተባለው ሰው ደግሞ በ1987 ስለ ራሱ ልምምድ ሲናገር አንድ ቅዳሜ ምሽት እየሰበከ ሳለ ተመስጦ ውስጥ እንደገባና ደመና ('የክብር ደመና' ይለዋል) እንደከበበውና በዚያው ጊዜ ከከተማው ውጪ የሆነ አንድ ቦታ ሁለት ሰዎች ሲያመነዝሩ ከተመለከተ በኋላ ሲነቃ ስብከቱን ካቆመበት እንደቀጠለ ተናግሮ ነበር። በመካከል ይህ ነገር ሲሆን 15 ደቂቃዎች ጠፍተው ነበር። በነ... ህ ጊዜያት ይህ ሰው ከአዕምሮው ውጪ ወይም በእርሱ አባባል 'በመንፈስ' ነበር።[11]

ከአዕምሮ መውጣትን መደገፍ ብቻ ሳይሆን ለመንፈሳዊም ሆነ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች አዕምሮን መስጠትን እንደ ስህተት የሚያዩ አስተማሪዎች አሉ። መንፈስ ቅዱስ እንጂ ሰው የሚያስተምረውን መቀበል ቀርቶ ለመስማትም እክፍል ውስጥ መግባት ደብተር ላይ መጻፍ፥ መጻሕፍት ማንበብ፥ መመራመር እንደ ክፉ ይወገዛል። በዝምታ ብቻ የምትባለውንና የሚሉህንም ሳትጠይቅ መስማትና መቀበል አለብህ። ሌላው ቀርቶ መጽሐፍ ቅዱስን እንኳ በስርዓት ማጥናት እንደመፈላሰፍ ይቆጠርና ሁለት ሦስት በተገናኙ ቁጥር አንድ ሰው ብቻ እንዲያነብና እንዲያስረዳ እንጂ በተለያየ የመረዳት ደረጃ ላይ ያሉ አማኞች አሳባቸውን እንዲያካፍሉ ማበረታታት

አሁንም 'የጭንቅላት ጅምናስቲክ' ይባልና እንደ ነውር ይቆጠራል።

ይህ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ.14:20 ከሚናገረው ትምህርት ጋር የማይሄድ ነው። በዚህ ክፍል ጳውሎስ የሚናገረው ነገር በአዕምሮ የበሰልን እንድንሆን ነው። ሮሜ.8:5 ውስጥ 'ያስባሉ' የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጭንቅላት ማሰብን ነው። ፊልጵ.2:2 እና 3:15 ውስጥም ያለው አሳብ የሚለው ቃል በአዕምሮ የሚታሰብን ነገር የሚናገር ነው። እግዚአብሔር በፍጹም አሳባችን ማለትም አዕምሯችን እንድንወደው ይሻል። (ማር.12:30) ቆላ.3:2 በላይ ያለውን እንድናስብ ያስተምረናል። በተጨማሪ ገላ.5:10 እና ሮሜ.8:6 ተመሳሳይ ትምህርት ይሰጡናል። ማወቅና ማመን ተቃራኒ ነገሮች አይደሉም። ጳውሎስ ቃልን በመጥቀስ ከአይሁድ ጋር ለመከራከርም ሆነ ለግሪክ ሰዎች ለማስረዳት አዕምሮውን ባይጠቀም ኖሮ ወንጌልን ባልሰበከም ነበር። (ሐዋ.17) እርግጥ ነው መንፈሳዊ ዕውቀት ከአዕምሮ ያልፋል፤ ይሁን እንጂ አዕምሮን አያዳፍንም። ጌታ አእምሮአችንን ይከፍተዋል እንጂ አይነጥቀንም፤ መንፈስ ቅዱስም አእምሮአችንን ያድሰዋል እንጂ አያስወግደውም።

1ዮሐ.4:1 መናፍስትን መርምሩ ይለናል። በእርግጥ እዚህ ቦታ መርምሩ የሚለው ቃል ከላይኛው ጋር በመጀመሪያው ቋንቋ ተመሳሳይ ባይሆንም አሳቡ ግን አስተውሉ የሚል ሆኖ ተቀራራቢ ነው። በዘመናዊዎቹ ይህን መሳይ እንቅስቃሴዎች ድፍርስ ያለ ቀውስ የሚፈጠረው ሰዎች ጤናማና አዕምሯዊ ምርምርንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስን በመጥቀስ እንዳይጠይቁ ስለሚደረጉ ነው። ቃሉ የሚለን ግን ሁሉን ነገር እንድንፈትንና መልካሙን እንድንይዝ ነው። (1ተሰ.5:19) ሰዎች የሚሰጧቸውን ትምህርቶች ሁሉ ከመቀበላቸው በፊት ማመንዘክ አለባቸው። አንድን ትምህርት ትክክል ወይም ስህተት መሆኑን የምናውቀውና የምንለየው ኤሌክትሪክ መሳይ ንዝረት ወይም ሙቀት ስለወረረን ወይም ጸጉራችን እስኪቆም ድረስ ቆዳችንን ስለጨመደደን መሆን የለበትም፤ ማለትም በአካላዊ ኹነታችን ላይ ከሚሰማን ስሜት ተነስተን መሆን የለበትም። ኬነት ኮፐላንድ የተባለ የቃል-እምነት ሰባኪ (ቃል-እምነት የሚባለው ትምህርት የምትናገረው ቃል ሁሉ የተፈጻሚነት ውስጣዊ ኃይል አለው የሚል ትምህርት ነው) እንዲህ ብሎ ነበር፤ "አማኞች በአመክንዮ (logic) መመራት የለባቸውም ...የኢየሱስ አገልግሎት በሎጂክ ወይም በአዕምሮ የተመራ አልነበረም።"[12] ይህ አባባል ግለሰባዊ ልምምዶችን ያለምንም ማመንታት እንድንቀበል የሚጋብዝ ከመሆኑም በላይ የጌታ አገልግሎት ኢ አመክንዮአዊ እንደሆነም ያስመስላል። ይህ ግን የራስን መስመር የሳተ ትምህርትና ልምምድ ከኢየሱስ አገልግሎት ጋር አመሳስሎ ለማመካኘት የተደረገ ሙከራ እንጂ ሌላ አይደለም። የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ስሜትን ኮርኩሮ ለማስደሰት ከሆነና

ለመቀበልና ላለመቀበል መለኪያው "ስሜት" የምንለው ነገር ብቻ ከሆነ ጸሎት ቤት ከቴአትር ቤት በብዙ የማይለይ ሊሆን ነው። ሰባኪዎቹም አዝናኝ ኮሜዲያን ሊሆኑ ነው። ክርስቲያኖች አዕምሯቸውን ዘግተው መንፈስን የሚመስል ስሜት ብቻ እንዲሰሙ የሚያደፋፍሩ እንዲህ ያሉ አስተማሪዎች የቤተ ክርስቲያንን አካልና የአማኞችን እምነት በማነጽ ፈንታ የሚበረብሩ ሊሆኑ ስለሚችሉ መጠንቀቅ ተገቢ ነው። 'ጭንቅላትህን አትስማው ወይም እንደ ባለ አእምሮ አታስብ፥ ቲዮሎጂህን ጣለው፥ ልብህ ውስጥ ብቻ የሚሰማህ ሙቀት መለኪያህ ይሁን' የሚሉ የቃሉ አስተማሪዎች ትንሽ ባልሆነ ጥንቃቄ መታየት አለባቸው። እንዲህ ያሉ ትምህርቶች ከቀጠሉ ማለትም የትምህርቶች ትክክለኛነት መለኪያ የልባችን ትርታና የስሜቶቻችን ግለት መጨመርና ያለመጨመር እንደሆኑ ከተወሰደ ስህተቶቹ አይቀጩም።

እግዚአብሔር ክርስቲያን ከሆንን በኋላ ጭንቅላታችንን ወይም አእምሮአችንን የማይፈልገው ቢሆን ኖሮ ጌታን የተቀበልን ቀን ቶዞ ሊያደርገን ይችል ነበር፤ ግን አላደረገንም ለምን? ምክንያቱም ጌታ ጭንቅላታችንን ወይም አዕምሯችንን በርግጥ ይፈልገዋል። ይህ ማለት መጽሐፍ ቅዱስን በጭንቅላታችን ብቻ ማስተማር ወይም መማር አለብን ማለት ነው? በፍፁም አይደለም። በአንዳንድ ትምህርት ቤቶችና ተቋሞች መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሥነ-ፅሁፍ እየተደረገ ይሰጣል፥ ከሚያስተምሩትም ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ መጽሐፉን እንጂ የመጽሐፉን ባለቤት የሚያውቁ አይደሉም። እነዚህ አስተማሪዎች መንፈስ ቅዱስ ስለማይኖርባቸው መጽሐፉን እንደ ተራ መጽሐፍ እንጂ እንደ መለኮታዊ ቃል አይቀበሉትም አይታዘዙትምም። በሌላ ቋንቋ ከጭንቅላት ለጭንቅላት ብቻ ነው የሚናገሩት። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚያስተምሩ አስተማሪዎች ወይም ከሰባኪዎች ወይም ከሌሎች አገልጋዮች ይህ አይጠበቅም። ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች ወይም ዳግም ተወልደውም በስጋዊነት የሚመላለሱ ከሆኑ ለሚያገለግሉበት ቤተ ክርስቲያን ችግር ፈጣሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲህ ያሉ አገልጋዮችን እመለየቱ ላይ ቤተ ክርስቲያን ጠንቃቃ ልትሆን ይገባታል።

የሚያሳዝነው እውነት ደግሞ 'ባለጭንቅላት ዕውቀት' እየተባሉ የሚወቀሱትና የሚከሰሱት አብዛኛውን ጊዜ በታማኝነት ጌታቸውንና የእርሱን ሕዝብ እያገለገሉ ያሉቱ መሆናቸው ነው። እነዚህ ሰዎች "በህልም ይህን አየሁ፥ በራዕይ ያ ተገለጠልኝ፥ ጌታ መልአኩን ልኮ እንዲህ አዘዘኝ፥ በተመስጦ ውስጥ ሳለሁ ይህ ታየኝ..." ሳይሉ ቃሉንና ቃሉን ብቻ ስላስተማሩና የራሳቸውን ወይም የሰዎችን ግላዊ ልምምድ ከቃሉ በታች ስላደረጉ ሊነቀፉና ሊሸሟጠጡ ባልተገባ ነበር።

የመገለጥስ ዕውቀት? እግዚአብሔር አዲስ ነገርን ይገልጣል? መገለጥ ሁለት አሳቦችን ሊያስተላልፍ ይችላል። የመጀመሪያው ፈጽሞ አዲስ ነገርን ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተጻፈ ነገርን ማግኘት ማለት ነው። የዚህ ዓይነት ነገርን መጠበቅ ለስህተት አሰራር መዳረግ ነው። እግዚአብሔር በቃሉ ላይ ከዮሐንስ ራዕይ ቀጥለንና ጨምረን የምንጽፋቸውን መገለጦች ከሐዋርያው ከዮሐንስ ራዕይ መጻፍ ጋር አቁሞአል። ቃሉ የታተመ ቃል ነው። ምንም አይጨመርበትም ምንም አይቀነስበትም። የሚጨምሩም የሚቀንሱም መርገም ተበይኖባቸዋል። ከቃሉ ጋር እኩል ሥልጣን ሊኖረው የሚሞክር መገለጥ ምንጩ ሰይጣን እንጂ እግዚአብሔር አይደለም። ዛሬ ዛሬ ሰዎች ለራሳቸው የሚመስላቸውን ነገር በአሳባቸው እያዩ ከእግዚአብሔር እንደተገለጠላቸው እያስመሰሉ መናገራቸው እየበዛ መጥቷል። አንዳንዶቹ ዘመናዊ አስተማሪዎችም በስህተት ይህን ነገር 'የምናብ ኃይል' (Power of imagination) ብለው ጠርተውታል።

"የምናብ ኃይል ከእስትንፋስ መለኮት ወይም አፊዎት (Inspiration) እና ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል ጋር እየተምታታ መጥቷል። ከሪያዊው መጋቢ ፖል ዮንጊቾ ሲናገር 'በምናብ ኃይል ነው እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው ስለዚህ ሰውም እንደ እግዚአብሔር 'ራብዓዊ መጠን' (fourth dimension) መንፈሣዊ አካል በመሆኑ እርሱም ክርስቲያን ይሁን ጣዖት አምላኪ በምናብ ኃይል የራሱን ዓለም መፍጠር ይቻለዋል' ብሏል።"[13] ይህ ጥልጥ ያለ ስህተት ነው። ይህ ምናባዊ መገለጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጥ ፈጽሞ አይደለም። ይህ ብቻ ሳይሆን ወደ ስህተት ልምምድና ወደ ስህተት ትምህርትም ይመራል።

ሌላ መገለጥ ደግሞ አለ ያም መብራራት መከሰት ወይም መፍታታት እንደማለት ያለ አሳብን የያዘ እውነት ነው። ይህም አብርሆት የምንለው ነው፤ Illumination ይባላል-በእንግሊዝኛ። ይህ የትምህርተ-መለኮት ቃል ሲሆን ትርጉሙ መንፈስ ቅዱስ የሚያደርገው በቃሉ ውስጥ የተጻፈውን እውነት የማብራት ተግባር ማለት ነው። ይህን ዓይነት ሥራ የሚሰራው መንፈስ ቅዱስ ራሱ ለአሰራሩ ጉጉ በሆኑ አማኞች ሁሉ ውስጥ ነው እንጂ በጥቂት የተለዩ ሰዎች ብቻ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ከሚሰራቸው ስራዎቹ አንዱ የጌታን ቃል ማስረዳት ወይም ማብራራት ነው። (ዮሐ.16:12-15) የእግዚአብሔር ቃል እንዲጻፍ ያደረገው መንፈስ ቅዱስ ራሱ እንደመሆኑ (2ጴጥ.1:20-21) ቃሉን በትክክል ሊገልጥ የሚቻለው እርሱ ብቻ ነው። ስለዚህ ማንም የእግዚአብሔር ቃል ተናጋሪ ቃሉን በሚያዘጋጅበትም ሆነ በሚያስተምርበት ወይም በሚሰብክበት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ በመደገፍ ማድረግ አለበት። ይህ ትክክለኛ የሆነው መገለጥ ነው። በእርግጥ እግዚአብሔር በህልምም ሆነ በራዕይ መናገር ወይም በወደደው መንገድ ለወደደው

የወደደውን መግለጥ ይችላል። ቃሉን የሚመስለው እውነተኛ መገለጥ ግን ይህ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ የተጻፈውን ቃል ለማብራራት በአማኞች ወይም በአገልጋዮች ውስጥ የሚያበራው ያ ብርሃን ነው።

መንፈስ ቅዱስ ይህን በሚያደርግበት ጊዜ ደግሞ እኒህን ሰዎች ከአዕምሯቸው ውጪ አያደርጋቸውም። የሚያስረዳቸውም አዕምሯቸውንም በመጠቀም ነው። ታዲያ የጭንቅላት ብቻ ዕውቀት አለ? አዎን አለ። አዕምሮን ፈጽሞ ያልነካና እንዲነካውም የማይፈልግ አዲስ መገለጥስ አለ? አዎን አለ። የቱ ነው ትክክል? ሁለቱም ስህተት ናቸው። ትክክለኛው መገለጥ ግላዊ ልምምድን ሳያጎሉ ቃሉን ለማብራራትና ሰዎችን ለመድረስ ተሳስተውም ከሆነ ለማረምና ለመመለስ በመንፈስ ቅዱስ ተደግፎ እውነቱን ማሳየት ነው።

እግዚአብሔር በህልምም ሆነ በራዕይ ተናግሮ ያውቃል። ያለ ማስተዋል እንጂ እኛ የጊታን እውነት ለማወቅ ከምንመኘው ይበልጥ እርሱ ለኛ እውነቱን ሊገልጥ ይመኛል። እግዚአብሔር በብዙ መንገዶች ተናግሯል። ለምሳሌ፤

- ለያዕቆብ፥ ለጌዴዎን፥ ለማርያም በመላእክት
- ለዮሴፍ፥ ለዳንኤል፥ ለፈርዖን በሕልም
- ለብልጣሶር በጣት
- ለበለዓም በአህያ
- ለአብርሃም፥ ለሙሴ በቃል
- ዛሬም በዘመናት መጨረሻ ላለነው ለኛ ደግሞ በልጁና በቃሉ ተናግሯል።

ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር መገለጥን ማግኘትና የራስን ምኞት በራስ መንገድ መቅረጽ ተመሳሳይ ነገሮች አይደሉም። የዘመናዊዎቹ አላሚዎችና ባለ ራዕዮች ስህተት በየጊዜው የሚያዩትን ሁሉ (ቅዠታቸውንም ጭምር) እንደ ፊልም እያስጠቆሩ ማሳተምን ስራዬ ብለው መያያዛቸው ነው።

እግዚአብሔር ያለማወቅን የሚጠላ ጌታ ነው። እግዚአብሔር እውቀትን ይወድዳል፥ ይሰጣልም። እንዲያውም የእውነተኛ እውቀት ምንጭ ራሱ እግዚአብሔር ነው። በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ 'እውቀትን መናገር' የተባለ የጸጋ ስጦታ አለ። በዘጸ.31:3 እና 35:31 የምናየው የኡሪ ልጅ ባስልኤል መንፈስ የሞላበት፥ ጥበብ፥ ማስተዋል፥ እውቀትም ያለበት ነበር። በኢሳ.11:1-2 ከእሴይ ግንድ ይወጣል የተባለው በትር የሚያርፍበት መንፈስ የእውቀትም

መንፈስ ነበር። ምሳ.1:7 እንደሚነግረን የጥበብ (ማለትም በዋናው ቋንቋ የእውቀት) መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው።

እግዚአብሔር እውቀትን የሚጠላ አምላክ አይደለም። እርሱ በባህርዩ አዋቂ ነው። (1ሳሙ.2:3) እኛም አምሳሉ ነንና ምንም እንደ እርሱም ባናውቅ ከባህርዩ ተካፍለን በትንሹም አዋቂዎች ነን። አዋቂነት ከእውቀት የሚመጣ ነው። ዳን.1:17 እና 2:21 እንደሚነግረን እርሱ ጥበብን ለጠቢባን እውቀትንም ለአስተዋዮች ይሰጣል። ሰለሞን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት ጥበብንና እውቀትን መጠየቁ እግዚአብሔርን አስደሰተው እንጂ አላስቀየመውም። (2ዜና.1:10-12) እግዚአብሔር እውቀትን አይጠላም። ሆሴ.4:6 እንደሚነግረን እግዚአብሔር እንዲያውም "ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቶአል አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ፤ የአምላክህን ሕግ ረስተሃልና እኔ ደግሞ ልጆችህን እረሳለሁ" ይላል። እዚህ ቦታ እውቀት የሚለው አሳብ የእግዚአብሔርን ሕግ እውቀት መሆኑ ጎልቶ ይነበባል።

የዘመናዊው የቃል-እምነት ትምህርት ምንጭ የሆነው ዊሊያም ኢ.ኬንየን ያስተምራቸው የነበሩት ትምህርቶች በሙሉ 'የመገለጥ ዕውቀት' በሚባለው ነገር የተሞሉ ነበሩ። እራሱን 'የመገለጥ ዕውቀት' የሚባለውን ቃል የቀመረውና ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበትም ኬንየን ነው። ኬንየን ዕውቀትን ሁለት ቦታዎች ይከፍልና አንዱን የመገለጥ ዕውቀት ሲለው ሌላውን ስሜታዊ ዕውቀት ይለዋል። እንደ ኬንየን አተረጓጎም ስሜታዊ ዕውቀት የሚባለው በአምስቱ የስሜት ኅዋሳት የምንረዳቸው ምድራዊ፣ ቁሳዊና አካላዊ ነገሮች ሲሆኑ መገለጣዊ ዕውቀት የሚባለው ደግሞ ሰማያዊና መንፈሳዊ መረዳት ነው። ብዙዎች ዲበ አካላዊ የስህተት ትምህርቶች (Metaphysical Cults) ሁሉ እነዚህን እውቀቶች ይለዩአቸዋል። የዘመናዊው ሚታፊዚካዊ የስህተት ትምህርቶች አባት ተብሎ የሚታወቀው ፊኒያስ ኩዊምቢ ለምሳሌ ይህን አበክሮ ያስተማረ ሰው ሲሆን ከተከታዮቹ አንዷ ሜሪ ቤከር ኤዲ የምትባለው ክርስቲያን ሳይንስ የሚባለው የስህተት ትምህርት ጀማሪ ናት። ይህ የስህተት ሃይማኖት አካላዊ ስሜትን በሙሉ (ለምሳሌ በሽታን) የሚንቅና እንዲያውም የሚክድ ትምህርት ነው። የሚታፊዚካዊ መገለጦች የመጨረሻ ዓላማ ሰውን ከሰውነት ወደ አምላክነት መለወጥ ነው። በመጀመሪያው ምዕት ዓመት ወደ ክርስትና ውስጥ ሰርጎ የገባ 'ግኖስቲሲዝም' የሚባል ስህተት ነበር። የዚህ የስህተት ትምህርት ዋና አሳብ ነገሮችን ሁሉ እሁለት መክፈልና ቁሳዊውን ዓለም ወራዳና ክፉ መንፈሳዊውን ደግሞ የከበረና መልካም በማድረግ ይህኛውን ማጥላላትና ያኛውን ማድነቅ ነው። እንግዲህ ይህ እውቀት ስሜታዊውንና አዕምሯዊውን በአቋራጭ ቀድሞ መንፈሳዊውን ለመድረስ የሚደረገው ትግል

በር ከፋች ነው።

> መጽሐፍ ቅዱሳዊው ዕውቀት በባህርዩ አካላዊ ብቻ ሳይሆን ሰዎች ያስተዋሉትና የተረዱትም አካላዊ በሆኑ ነገሮች ነበር። ቃል ስጋ መልበሱን ለመረዳት ሐዋርያት አካላዊ ሕዋሳትን ተጠቅመዋል፤ ዮሐንስ "ክብሩን አየን" አለ። (ዮሐ.1:14) ጴጥሮስ ደግሞ "የእርሱን ግርማ አይተን" አለ። (2ጴጥ.1:16) እንዲሁም 2ጴጥ.1:18 ደግሞ "እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋር ሳለን ይህን ድምጽ ከላይ ሲወርድ ሰማን" ይላል ሐዋርያትም ስለ ሕይወት ቃል ያዩትን፥ የሰሙትን፥ በእጆቻቸውም የዳሰሱትን መስክረዋል። (1ዮሐ.1:1) የእግዚአብሔር ቃል የመጨረሻ መገለጫ የሆነው የኢየሱስ ስጋ መልበስና ሞት እንኳ በባህርዩ አካላዊ ሆኖ መረዳት የተቻለውም በአካላዊ መንገድ ነው።[14]

በ1ቆሮ.8:2-3 እንደተጻፈው ዕውቀታችንን ለዕውቀትነቱ ብቻ ከተጠቀምንበት ያስታብየናል። ፍቅር ከኖረበት ግን ያንጻል። ስለዚህ እውቀት ያለው ያወቀውን ያህል ፍቅርን የመግለጥ ኃላፊነትም አለበት።

# እባብ ያዦቹና መርዝ ጠጪዎቹ

አንዳንድ አስተማሪዎች ማር.16:17-18ን አማኞች ሁሉ መለማመድ እንዳለባቸው ሲያስተምሩ ወይም ሲጽፉ ከፊሉን ብቻ ያጎሉና ከፊሉን እስከመኖሩም ይዘነጉታል። የተጻፉት አማኞችን የሚከተሉ አምስት ምልክቶች በጌታ ስም አጋንንትን ማውጣት በአዲስ ቋንቋ መናገር፥ እባቦችን መያዝ፥ የሚገድል ነገር ጠጥቶ ያለመጎዳት እና በድውዮች ላይ እጆችን መጫንና የድውዮቹም መዳን ናቸው። ለምሳሌ መንፈስ ቅዱስ በተሰኘው የአማርኛ ዕትም ስለዚህ ክፍል ስጦታዎች ጸሐፊው ሲናገሩ "ጌታ ኢየሱስ በማር.16:17 'ያመኑትም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል' በማለት ስለ ልዩ ቋንቋ፥ ስለ ፈውስ፥ ስለ አጋንንት ማስወጣት ይናገራል፤ ይህ ሥልጣን ለሐዋርያት ብቻ የተሰጠ እንደሆነ አይናገርም።"[15] ብለዋል። በእርግጥ በዚህ ክፍል ረገጥ ተደርጎ እየተነገረ ያለው ስጦታዎች ለተወሰኑ ሰዎች ወይም ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ያለመሰጠታቸው ነው፤ እንደዋዛ ቢሆንም ግን ከአምስቱ ሁለቱ መዘለል አልነበረባቸውም። እንዲህ የሚያደርጉት ማለትም ሲጽፉ ሲያስተምሩም ሆነ

ሲሰብኩ ከዝርዝሩ ውስጥ በአንዱ ወይም በሁለቱ ብቻ የሚያተኩሩ ብዙ ናቸው። ለብዙዎቹ አጠቃቀስ ደረጃ ቢሰጠው በአዲስ ቋንቋ መናገር በአንደኛ፥ ፈውስና አጋንንት ማውጣት በሁለተኛ ሲጠቀስ፥ እባብ መያዝና መርዝ መጠጣት ወይ የመጨረሻ ደረጃ ይሰጣቸዋል ወይም እንዳልተጻፉ ሁሉ ይረሳሉ።

ስለዚህ ጥቅስ ጥቂት ነገሮችን መመልከት አስፈላጊ ነው። በመጀመሪያ ማር.16:1-8 እንጂ ከዚያ በኋላ ያሉት ጥቅሶች ቀደምትነት ባለቸው መጽሐፍ ቅዱሶች ወይም ቀደምትነት ባላቸው ትርጓሜዎች አይገኙም። አንዳንድ ዘመናዊ ትርጓሜዎችም በቅንፍ ውስጥ ነው የሚያስቀምጡት። የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ሁሉ ይህን ያውቃሉ። ይህን እውነት ማወቁ አስፈላጊ ይሁን እንጂ ይህ ክፍል የእግዚአብሔር ቃል አይደለም ብለን ላለመቀበል ልባችን የሚከጅል አይመስለኝም። ሌላው ማየት ያለብን ነገር እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል ነው የተባልነው እንጂ ትከተሏቸዋላችሁ አልተባልንም። ስለዚህ ይህ ጥቅስ እባቦችን ለመያዝ በጌታ በኢየሱስ ስም ድንጋይ መፈንቀል እንዳለብን አያስተምረንም። ሌላው ያመኑትንም ሲል በወል መናገሩንና ያመነውን እያንዳንዱን ወይም ያመኑትንም ሁሉ እንዳላለ ማስተዋል አለብን። እኒህን ስጦታዎች ከዐውዱ ሳናወጣና ከሌሎችም ተመሳሳይና ተቀራራቢ ጥቅሶች ጋር በማወዳደር መሆን አለበት ማጥናት ያለብን።

ይሁን እንጂ በአንፃሩ ደግሞ እነዚህ የታለፉቱ ሁለቱም ስጦታዎች ላይ ብቻ የሚያጎሉና እነርሱን ብቻ የሚለማመዱም ደግሞ አልጠፉም። በዚህ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ አካባቢ ጆርጅ ሄንስሊ የተባለው ሰው በአሜሪካ ውስጥ በቴነሲ፥ በኬንተኪ፥ እንዲሁም በአሃዮ ግዛቶች ያገለግል በነበረ ጊዜ ይህን የእባብ መያዝ ምልክት በየስብሰባው ይፈጽም ነበር። የዚህ ሰው ሕይወት በውጣ ውረዶች የተሞላና መንፈሳዊ ሕይወቱም ብዙ አጠያያቂም ቢሆንም አገልግሎቱን እያቋረጠና እየቀጠለ ቆየ። ሄንስሊ በመስከረም 1945 በቴነሲ ግዛት ሲያገለግል ሉዊስ ፎርድ የተባለው የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በእባብ ተነድፎ ሞተ። ይሁን እንጂ ይህ አገልግሎቱን አላስቆመውም። የቴነሲ ግዛት በ1947 የዚህ ዓይነቱን አድራጎት የሚከለክል ሕግ ቢያወጣም እነዚህ ሰዎች እየተቀጡም ማድረግ ቀጠሉ እንጂ አላቆሙም። ጆርጅ ወደ ፍሎሪዳ ግዛት ሄዶ በማገልገል የመጨረሻዎቹን ጊዜያት አሳለፈ። በዚሁ ዓመት ሐምሌ 24 ቀን የመጨረሻ አገልግሎቱን ባገለገለ ዕለት ስብሰባውን የተካፈለ አንድ ሰው ሲናገር፤

> ሄንስሊ በዕለቱ በልሳን እየተናገረ ይሰብክና 'እምነት፥ እምነት ሁሉን ይፈውሳል' ይል ነበር ደጋግሞ። ...ከዚያ አምስት ጫማ ርዝመት የነበረውን መርዘኛ እባብ ያ ጥቂት ሰዎች

የነበሩበት ጉባዔ እያየ አወጣና በአንገቱና በእጁ ላይ ጠመጠመው። ከ10 ያህል ደቂቃ በኋላ ሄንስሊ እባቡን ወደ ሳጥኑ እየመለሰ ሳለ ትልቁ እባብ መርዛማ ጥርሱን በቀኝ እጁ ላይ አጠለቀው። በገራ እጁም እባቡን አላቅቆ ወደ ሳጥኑ አስገባው። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥም ሕመም አጣደፈው። ቢሆንም ምንም ሕክምና ሊወስድ አልፈለገም። በትልቅ ስቃይ ሆኖ ደም እያስመለሰው ቆየ። የመጨረሻ ትንፋሹን ከመተንፈሱ በፊት ወደኔ ዘወር ብሎ 'እዚህ መሃል ያለ አንድ ሰው ፍርሃት ባይይዘው ኖሮ ይህ እባብ አይነድፈኝም ነበር' አለኝ።[16]

ጆርጅ ሄንስሊ ይህን ያደረገና ይህ የደረሰበት የመጀመሪያና የመጨረሻ ሰው አይደለም። ከላይ የተጠቀሰው ቃል ከተወሰደበት መጽሐፍ መጨረሻ አካባቢ የጥያቄና መልሶች ገጾች አሉ። ከጥያቄዎቹ አንዱ 'ስንት እባብ ያገሩ በእባብ ተንድፈው ሞተዋል?' የሚል ነው። ለዚህ የተሰጠው መልስ፤

ከአምልኳቸው ሕጋዊ ያለመሆን ቤተ ክርስቲያኖቹ ከማንም ተቆጣጣሪነት ነፃ የሆነ አመራርና አሰራር የተነሳ እንዲሁም ቀደም ሲል የሆኑትን ነገሮች ለማወቅ አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳና በየቦታው የሚጻፉትን ዘገባዎች ከማጠናቀሩ አስቸጋሪነት የተነሳ ትክክለኛ አሃዝ ማቅረብ ያስቸግራል። ቢሆንም እስቲቨን ኪን እንደዘገበው እስከ ኤፕሪል 1990 ድረስ 69 ሰዎች ሞተዋል። በነዚህ ላይ አባቱ (በቤተ ክርስቲያን አምልኮ) መርዝ ጠጥቶ ከሞተ ከ18 ዓመታት በኋላ ጁላይ 13/1991 የሞተው ጂሚ ሬይ ዊሊያምስ እና በዲሴምበር 2/1991 የሞተው ሬይ ጆንሰን ይጨመሩበታል።[17]

ቻርልስ ፕሪንስ ሌላው ሰው ነው። አባቱ ቅድስና በሚባል ቤተ ክርስቲያን ያገለግል የነበረ ሰው ሲሆን እርሱም ማር.16:17-18ን አበክሮ የሚለማመድ ሰው ነበር። ቻርልስ ግን አደግ ሲል መንፈሳዊነቱን ተወ። በኋላ ግን በአንድ ምክንያት ተለወጠ። መለወጡ ድንገተኛ ነበር። ጌታን ትቶ በነበረባቸው ጊዜያት እህቱና ወንድሙ ይጸልዩለት ነበርና ሊሳቡት ሄዱ። መንፈሳዊ ሕይወቱም ተሻሻለ። በዚያው ሰሞን አንድ ራሱን ሊገድል ሲሞክር እጁ የተቆረጠበት ሰው እጁ እንዲመለስለት ሊጸልዩ ሃስቱም ተወያዩ። ከዚያ በፊት ግን እምነታቸውን በሌላ ነገር ለመፈተን ተስማሙና በጸሎት አንድ የቡና ስኒ እንዲንሳፈፍ ሙከራ አደረጉ። ይህ ሙከራቸው ግን አልሰራም። ስለዚህ የእጅ መቀጠሉንም ጸሎት አቆሙ። የቻርልስ ሕይወቱ ግን ከዚህ በኋላ እንደ ቀድሞው አልሆነም። መንፈሳዊ ሕይወቱ ማደግ ጀመረ። በኋላም ንብረቱን ሽጦ ከፊሉን ለሚስቱ

ሰጠና ከፊሉን ደግሞ ለድሆች ሰጥቶ ሲያበቃ ሰባኪ ሆነ።

አንድ ቀን እቤተ ክርስቲያን ሳለ የእምነቱን ግደግ የመፈተን ምኞት አድሮበት አንድ አሳብ መጣበትና አቋርጦ ወደ ቤቱ ሄዶ መኝታ ቤቱን ዘጋውና ለሰዓታት ጸለየ። ከዚያም አንድ ጠርሙስ አንስቶ በውስጡ ያለውን መርዝ በሙሉ ጨለጠው። በዚያ ሰዓት የሆነውን እራሱ ሲናገር፤

> ከከንፈሮቼ እስከ ሆዴ ድረስ ተቃጠልኩ። ድምጾች ይሰሙኛል። እነዚህ ድምጾች እየሞትኩ ስለሆነ ብተኛ ከንቱ እንደሆነ ይናገሩኛል። መሞቴ ስለሆነም ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድም ከንቱ እንደሆነ ይነግሩኛል። እየተናገረኝ ያለው ሰይጣን እንደሆነ ገባኝ። አልጋዬ ላይ ተጋደምኩና መጽሐፍ ቅዱሴን ማር.16 ላይ ከፈትኩና 17ኛውን ጥቅስ ሳነብ እሳቱ ጠፋ። እንደማልሞትም አወቅኩና ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመልሼ ድምጼን ከፍ አድርጌ በጩኸት ተናገርኩ።[18]

የቻርልስ አገልግሎት ቀጠለ። በእሁድ የአምልኮ አገልግሎቶቹ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፥ እባቦችን መያዝና እስትሪክናይን የተባለ ኃይለኛ መርዝ መጠጣት እየተደባለቁ መጡ። በ1980ዎቹ የመጀመሪያ አጋማሽ በቅድስና አብያተ ክርስቲያናት ዝነኛ እየሆነም መጣ። ይሁን እንጂ በሰባት የተለያዩ ጊዜያት በእባቦች እየተነደፈ የአልጋ ቁራኛ ሆኖም ነበር። በነሐሴ 21/1985 በግሪንስቪል ቴነሲ ባለችው የእግዚአብሔር ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን በምትባለው እየሰበከ ሳለ ከሳጥኑ ውስጥ አንድ መርዘኛ እባብ አወጣ። ገና ከማውጣቱም እባቡ ግራ እጁን በአውራና በአመልካች ጣቱ መካከል ነደፈው። በዚያ ዕለት መነደፉን ችላ ብሎ እባቡንም አትሮንሱ ላይ አድርጎ እስትሪክናይን የተቀዳበትን ብርጭቆ አልፎ አልፎ እየጠጣ በየጣልቃውም በአምልኮ መልክ እየጨፈረና እየደነሰ ስብከቱን ጨረሰ። በመጨረሻ ተዝለፍልፎ ወደቀ። በቤተ ክርስቲያኑ የነበሩት ሰዎች ጥያቄ 'ሳይሻለው ምን ያህል ይቆያል?' የሚል ነበር እንጂ እንደሚሞት የተጠራጠሩም አልነበሩም። ይሁን እንጂ ከብዙ ሰዓታቶች ስቃይ በኋላ በማግስቱ ሰኞ ነሐሴ 22/1985 ሕይወቱ አለፈች።

ማር.16:17-18ን ስናጠና ከላይ መግቢያው ላይ ያሉትን አሳቦች መዘንጋት የለብንም። በተጨማሪም እግዚአብሔር በሁሉን ቻይነቱና በመለኮታዊ አሰራሩ በወደደው መንገድ ጣልቃ ሊገባ እንደሚችል መርሳት የለብንም። እርሱ በወደደው ጊዜ ለልጆቹ ልዩ ኃይል ሊሰጣቸው ይችላል። እባብ መያዝን በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈልን ታሪክ ይገኛል። በሐዋ.28:3-6 ተጽፎ የምናገኘው ጳውሎስ በእፉኝት (በእባብ) ተነድፎ ነበር።

እፋኝቷ ከሙቀት የተነሳ ነው ወጥታ የነደፈችው እንጂ ጳውሎስ ሆን ብሎ የሚያምነው ጌታ ቃሉን የሚጠብቅ መሆኑን ለማስመስከር ብሎ አውጥቶ አልያዛትም። ተነድፎም አብጦ ያለመውደቁንና ያለመሞቱን የአገሬው ሰዎች ሲያዩ አሳባቸውን ለወጡ። መርዝን በተመለከተ ምንም የተጻፈልን የአዲስ ኪዳን ማረጋገጫ ባይኖርም እግዚአብሔር ይህም ይቻለዋል። ይሁን እንጂ እኛ ራሳችንን ለአደጋ አጋልጠን እየሰጠን እግዚአብሔርን መፈታተን እንደማይገባን አማኞች ማስተዋል አለብን። (ዘዳ.6:16)

## ቃል-እምነት

ቃል-እምነት (Word-Faith) የሚባለው ትምህርት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየሰፋ የመጣ ነው። የዚህ ትምህርት ዋና አሳብ የምንናገረው ነገር ሁሉ የመከናወን ውስጣዊ የሆነ የራሱ ኃይል አለው ስለዚህ ጥሩ ነገር ስንናገር ጥሩ ነገር ይሆንልናል መጥፎ ነገር ብንናገር ደግሞ የተናገርነው መጥፎ ነገር ይደርስብናል የሚል ነው። እንደዚህ ትምህርት አባባል ለመፈወስ ቢያምህም 'ጤና ነኝ፥ ደህና ነኝ' ማለት አለብህ። ሀብታም ለመሆን ምንም እንኳ በቁሳዊ ነገሮች ድሃ ብትሆን 'ሀብታም ነኝ፥ ሁሉ አለኝ፥ ምንም የጎደለኝ የለም' እያልክ መለፈፍ አለብህ። ሌላው የዚህ ትምህርት ስም 'ተናግረህ ተቀበል' (Name-it-and-claim-it ወይም Confess-and-possess ወይም Blab-and-grab) በመባል ይታወቃል።

ቡድሂስቶች አንድን ቃል ወይም ሐረግ ደጋግሞ በመናገር አንድን ነገር እንዲሆን ወይም እንዳይሆን ማድረግ የሚያስችል ተመሳሳይ ፍልስፍናዊ ትምህርት አላቸው። በነርሱ እምነት ይህ ልምምድ 'ሶካ-ጋካይ' ይባላል። አስቀድሞ ፖል ዮንጊ ቾ በኋላም ስሙን ቀይሮ ዴቪድ ቾ የተባለው ኮሪያዊው መጋቢ ይህን ሕግ የተፈጥሮ ሕግ እንደሆነና እነዚያ ክርስቲያን ያልሆኑ በሰይጣን ኃይል ስር ያሉ ሰዎች የዚህን አሰራር ተረድተው ከተጠቀሙበት እኛ ክርስቲያኖቹማ አብልጠን ለምን አንጠቀምበትም በማለት ይህን ትምህርት ከሚያራምዱት ሰዎች አንዱ ነው።[19] ይህ የቾ ትምህርት በኛ አቆጣጠር በ70ዎቹ ውስጥ ተተርጉሞና በካሴት ተራብቶ ይሸጥ የነበረው 'የመናገር ሕግ' የተባለው ትምህርት ነው። የምሥራቃውያንን ኃይማኖት መርማሪዎችና የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ (The New Age Movement) አጥኚዎች ይህ ትምህርት ከቡድሂዝም ጋር የተቆራኘ መመሳሰል እንዳለው ያምናሉ።